# የነገረ ሃይማኖት ትምህርት መግቢያ


## አዘጋጅ፡ መምህር ምስጢረ ሥላሴ ማናዬ


## ቀን፡ ፲፱መጋቢት፳፻፲ዓ.ም

## ቦታ፡ ፕሪቶርያ - ደቡብ አፍሪካ

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዱ አምላክ አሜን።**

## መግቢያ

*ይህ አጭር ጽሁፍ የክረምት ተተኪ ሰባኪያነ ወንጌል ስልጠና የነገረ ሃይማኖት ማጠቃለያ ጽሁፍ ነው። ሁሉም ነገር መደምደሚያ እና ማጠቃለያ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር ፍጥረትን በመጀመሪያው ቀን በእለተ እሁድ ጀመረ በስድስተኛው ቀን የፍጥረትን ሁሉ መደምደሚያ ሰውን ፈጥሮ ፍጥረቱን አጠቃለለ። ማጠቃለያ ማለትም መደምደሚያ መቋጫ ማብቂያ ማጠናቀቂያ ማለት ነው። በጅምር የቀረ ሁሉ ደስ አያሰኝም። ያለቀ የተጠቀለለ ደግሞ ደስ ያሰኛል። ጀምሮ መጨረስ አስፈላጊ መሆኑን አበው እንዲህ ብለው ይገልጡታል "የ ሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ"።*

*የሺ ፍልጥ ትንሽ ልጥ እንዲያሻው ይህ ክረምት ላይ የተሰጠው ትልቅ የነገረ የሃይማኖት ትምህርት ጥቂት ማጠቃለያ አስፈልጎታል። ዝርው ሆኖ እንዳይቀር ሰብስብ አድርጎ አስሮ በልቡናችን ትከሻ ላይ መሸከም እንችል ዘንድ ነው። በልቡናችን ትከሻ ላይ የተሸከምነው ትምህርተ ሃይማኖት ያልሆነ ቦታ ላይ እንዳይበተን ተገቢው ቦታ መርጠን እንድናስቀምጠው ነው። በሌላ መልኩ ማጠቃለያ ማለት የተማርነውን ማሳሰቢያ ማስገንዘቢያ ወደ ኋላ መለስ ብለን የተማርናቸውን ቁም ነገሮች መመልከት የሚያስችል ማስታወሻ ነው።*

*ወይም ስርዋጽ ስንማር የጎደለ መሙያ ማስተካከያ የተጣመመ ካለ ማቅኛ በውስጣችን የቀረም ጥያቄ ካለ መመለሻ በአጠቃላይ የወሰድነው ትምህርት ማካካሻ ደጋፊ ነው። ስለዚህ የተማርነውን ትምህርት ከመሰረቱ እስከ ጉልላቱ በደንብ አጣርተን ካወቅን የድንቁርና ዝናብ እንዳያበሰብሰን የክህደት ዋእየ ፀሐይ እንዳያቃጥለን መከላከል እንችላለን። በዚህ ማጠቃለያ ሃሳብ በምዕራፍ አንድ ነገረ ሃይማኖትን የማጥናት ዓላማ እና ጥቅም፤ ሃይማኖት ምንድን ነው?፤ ህልዎተ ፈጣሪ ፤ የሥነ_ፍጥረት ምንነት፤ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮች፤ ነገረ እግዚአብሔር። በምዕራፍ ሁለት የምሥጢር ፍቺ በቤተ ክርስቲያን፤ ምሥጢረ ሥላሴ ፤ ምሥጢረ ሥጋዌ፤ ምሥጢረ ጥምቀት፤ ምሥጢረ ቁርባን፤ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ተዳስሰዋል። በአግባቡ አንብበን እንድንጠቀምበት እግዚአብሔር ይርዳን።*

# ምዕራፍ አንድ

# የነገረ ሃይማኖት ትምህርት መግቢያ

## 1፡1 *ነገረ ሃይማኖትን የማጥናት ዓላማ እና ጥቅም*

### *ሃይማኖትን የማጥናት ዓላማ እና ጥቅሙ*

*ሃይማኖት ሰው እና እግዚአብሔር የሚገናኙበት መንገድ ነው። ሰው በሃይማኖት ወደ ፈጣሪው ሲቀርብ ፈጣሪም ወደሰዎች ይቀርባል።"ቅረብዎ ለእግዚአብሔር ወይቀርበክሙ ፤ እግዚአብሔርን ቅረቡት ይቀርባችኋል" ያዕ "ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ ፤ ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችኋል"መዝ 33፡ 5 ። ሃይማኖት ሰው እና እግዚአብሔር የሚግባቡበት ቋንቋ ነው ። ሰው ነገረ ሃይማኖትን አጥንቶ አዲስ ነገር ለመፍጠር ሳይሆን ሃይማኖቱን አውቆ ከፈጣሪው ጋር ተገናኝቶ በንስሓ ተጠግቶ የመንግስቱ ወራሽ የስሙ ቀዳሽ ይሆን ዘንድ ነገረ ሃይማኖትን ያጠናል። ማጥናት አንድን ነገር በጥልቀት ለመረዳት የምናደርገው ጉዞ ነው። ሃይማኖትን እንደ ሌላው ሥጋዊ ሃሳብ አጥንተን ብቻ የምናውቀው ባይሆንም ሃይማኖትን ለመገንዘብ መጻሕፍትን ማገላበጥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን መጠየቅ እና ሃይማኖቱ ከቀና ምግባሩ ከፀና መምህር ተምሮ አውቆ ጠንቅቆ ለመጓዝ ነው። በየጊዜው ዘመን ከወለዳቸው እና ከሚያመጣቸው ሃይማኖት መሰል አመለካከቶች ራስንም ወገንንም ለመጠበቅ ነገረ ሃይማኖትን ማጥናት አስፈላጊ ነው። ነገረ ሃይማኖትን ማጥናት በሃይማኖት የሚገኘውን መንፈሳዊ ጥቅም ለማወቅ ይረዳል። ነገረ ሃይማኖትን በአግባቡ ያጠና ሰው ቤቱን በዓለት ላይ የመሰረተ ሰውን ይመስላል። ነፋስ ቢመታው ጎርፍም ቢጎርፍ መቋቋም እንዲችል ነገረ ሃይማኖትን ያጠና ሰው መከራ ቢመጣ ፈተና ቢበዛ ሃይማኖቱን ጋሻ አድርጎ ፈተናውን ድል እየነሳ ይጓዛል "ነፍሁ ነፋሳት ወውህዙ ወኃይዝት ወገፍእዎ ለውእቱ ቤት ወኢወድቀ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሳረረ ፤ ነፋሳት ነፈሱ ጎርፎችም ጎረፉ ያንን ቤት ገፉት አልወደቀም በዓለት ላይ ተመስርቷል እና "ማቴ 7፡27 28።*

*ነገረ ሃይማኖትን ያጠና ሰው ከሞቀው ከደመቀው ዘፋኝ አይሆንም። ማንም ወደፈለገው አይነዳውም። ያመነውን አምላክ ያውቃልና ሃይማኖቱንም ይገነዘባልና። ምን ማድረግ ምን መሥራት እንዳለበት አውቆ እና ተረድቶ በሃይማኖቱ ጸንቶ ይኖራል። ነገረ ሃይማኖትን ያጠና ሰው በሃይማኖት የነበሩ ሰዎች ከፈጣሪያቸው ያገኙትን ጸጋ እና በረከት አውቆ እግዚአብሔር በሃይማኖት ጸንተው መከራውን ታግሰው ከነደደ እሳት ገብተው ከአላውያን መኳንንት ከከሃድያን ነገሥታት ጋር በተጋደሉት ተጋድሎ ሲረዳቸው እሳት ሲያጠፋላቸው ነበልባል ሲያበርድላቸው ተአምራት ሲያደርግላቸው እንደነበረ ዛሬም እኔን በመከራዬ ውስጥ ይረዳኛል ብሎ እምነቱ እንዲጸናለት ያደርጋል።*

## 1፡2 *ሃይማኖት ምንድን ነው?*

*ሃይማኖት በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል አንድነት ይኖር ዘንድ ለቅዱሳን አበው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትልቅ ስጦታ ነው። ይህ ትልቅ ስጦታ የሰው ልጅ ከተቀበለው ጊዜ ጀምሮ ሃይማኖቱን ለመጠበቅ የክብር አክሊልን ለመቀዳጀት በገድል የኖረ በደም የታተመ ሥጦ ታ ነው "ወአስተበቁአክሙ አህዊነ ከመትትቀነይዋ ለእንተ ተውህበት ለቅዱሳን ሃይማኖት፤ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠች ሃይማኖት ትጋደሉ ዘንድ እማልዳችኋለሁ" ይሁዳ 3። ለቅዱሳን አበው የተሰጠች አበው ከእግዚአብሔር የተቀበሏት በተጋድሎ የኖሩላት የሞቱላት መከራ የተቀበሉባት ከህግር ምድረበዳ ከዘመድ ባዳ ይሻላል ብለው የተሰደዱላት ናት ሃይማኖት።*

ይህቺውም ነቅእ የሌለባት ጥርጥር ያልተገኘባት ቀጥተኛ መንገድ ናት። አበው ወደ እግዚአብሔር የተጓዙባት ውሉድም አበውን መስለው አምነው የተቀበሏት ቀጥተኛ መንገድ ናት"ርትዕት ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ ፤ የቅዱሳን አባቶቻችን ሃይማኖታቸው የቀናች ናት" እንዲል ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ። "ሃይማኖት እንተ እምኀበ  አብ ተፈጥረት ኀበ ወልድ ታበጽህ ወኀበ መንፈስ ቅዱስ ትትፌጸም፤ ሃይማኖት በአብ ትጀመራለች ወደ ወልድ ታደርሳለች በመንፈስ ቅዱስ ትፈጸማለች" እንዲል ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊ።

ሃይማኖት ሰው ፈጣሪውን ደስ የሚያሰኝበት ከሞት የሚያመልጥበት ከመከራ  ሥጋ ከመከራ ነፍስ የሚያመልጥበት ፤ ባህር የሚከፍልበት ፤ ድውይ የሚፈውስበት ነው። "በተአምኖ  ፈለሰ ሄኖክ ከመ ኢይርአዮ ለሞት ወኢተረክበ እስመ ከበቶ  እግዚአብሔር ፤ ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ እግዚአብሔር ስለወሰደው አልተገኘም ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፡ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም" ዕብ 11፡5 ዘፍ 5፡22

ሃይማኖት ተስፋ የምናደርገውን ነገር የሚያስረግጥ የተሰወረውን የሚገልጥ የራቀውን የሚያቀርብ የጠመመውን የሚያቀና የጎደለውን የሚሞላ በጨለማ ውስጥ የሚያበራ ነው። "ሃይማኖትሰ ጥይቅት ይእቲ ለዘይሴፈዋ ፤ እምነት ተስፋ  ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ ነው" ዕብ 11፡1 አበው ከጥፋት ውሃ የዳኑባት፤ ከሰዶም ወጥተው በከተማዋ ከታዘዘው መቅሰፍት ከወረደው እሳት ያመለጡባት ሃይማኖት ናት ዘፍ 6፡1፤ 7፡1፤ 8፡1፤ 19፡19

ሃይማኖት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን መንግስተ ሰማያትን ህይው ከመ መላዕክትን ሕይወተ ልቡናን ገንዘብ የምናደርግባት ናት። ሃይማኖት የሰው ልጆች ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስ የሚያገኙባት፤ ብዙዎች ከደዌ ሥጋ የዳኑባት ከደዌ ነፍስ ነጻ የወጡባት፤ ከማእሰረ ህማም ከማእሰረ ኃጢአት የተፈቱባት ፤ ዓይን የሌላቸው ዓይን እጅ እግር የሌላቸው እጅ እግር ያገኙባት፤ ማየት ያልቻሉ ያዩባት መስማት የተሳናቸው የሰሙባት፤ ሃንካሳን እንደ እንቦሳ እየዘለሉ ፈጣሪያቸውን ያመሰገኑባት ብቸኛ መንገድ ሃይማኖት ናት።

ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች ፈጣሪያቸውን ሲያስደንቁ ቅዱስ መጽሐፍ ያስነብበባል። "ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀ ለተከተሉትም እንዲህ አለ እውነት እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም" ማቴ 8፡10። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ድንቅ ተአምራት እያደረገ  በምድር ሲመላለስ ድውያንን ሲፈውስ የሰዎችን እምነት አይቶ  ተመልክቶ ይፈውሳቸው እንደነበረ እናያለን። "ወርእዮ  እግዚእ ኢየሱስ ሃይማኖቶሙ ይቤሎ ለወሬዛ ተሀድገ ለከ ኃጢአተከ ፤ በአልጋ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አመጡ ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን አንተ  ልጅ አይዞህ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው" ማቴ 9፡2 ድንቅ ሥራው በሰፊው በተገለጠበት ሁሉ እምነትህ አድኖሃል እምነትሽ አድኖሻል እያለ የሚናገረው በሰው ልጆች ድኅነት ውስጥ ሃይማኖት ቁልፍ ነገር መሆኑን ያስገነዝበን ዘንድ ነው። "ልጄ ሆይ አይዞሽ ሃይማኖትሽ አድኖሻል" ማቴ 9፡22 ። በዚህ መሰረት የድህነት መንገድ ነው። የታመሙት ሁሉ ወደ ሕይወት የሚጓዙበት፡ ከፈጣሪያቸው ተገናኝተው ምህረቱን ቸርነቱን አግኝተው፤ በእርሱ አምነው ጸንተው ፤ ከአምልኮተ ጣኦት ርቀው፤ ከኃጢአት ባርነት ከዲያቢሎስ ቁራኝነት ተለይተው፤ ከርኩሰት ነጽተው የሚመላለሱበት ነው።

ሃይማኖት አበው ደመና ጠቅሰው ካሰቡት ደርሰው የፈጣሪያቸውን ክብር እንዲገልጡ ፤ የራቁ አሕዛብን ወደ እግዚአብሔር መንገድ እንዲያመጡ ጉልህ ድርሻ  ነበረው። አሁንም አለው። ሃይማኖት ቅዱሳን ሐዋርያት

ድውያንን እንዲፈውሱ ሙታንን እንዲያስነሱ አጋንንትን ድል እንዲነሱ የረዳቸው ነው። እባቡን እንዲረግጡ ጊንጡን እንዲጨብጡ፣ ከመከራ እንዲያመልጡ፣ የታሰሩበት ሰንሰለት ረግፎ ከወህኒ እንዲወጡ ሃይማኖት መሰረት ነበር። እግዚአብሔርን እንዲከተሉ ፈጣሪያቸውን እንዲመስሉ ያስቻላቸው ሃይማኖት ነው። ጠላቶቻቸውን እንዲወድዱ ራሳቸውን እንዲክዱ በፍቅረ እግዚአብሔር እንዲናደዱ ያደረጋቸው ሃይማኖት ነው።

“ወናሁ ወሀብኩክሙ ስልጣነ ትኪዱ ዲበ አቃርብት ወዲበ ኩሉ ኃይለ ፀላኢ፣ እባቡን ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ትሰለጥኑ ዘንድ ስልጣን ሰጠኋችሁ ” ሉቃ 10:17 ርስት ጉልታቸውን ቤት ንብረታቸውን ዘመድ አዝማዳቸውን እንዲተው ፣ ዓለምን እንዲንቁ ፣ ከክብረ ዓለም እንዲርቁ ያስቻላቸው ሃይማኖት ነው። “ንህነ ሀደግነ ኩሎ ወተሎናከ ምንተ እንከ ንረክብ፣ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ምን እናገኝ ይሆን ? ”ማቴ 19:26።
ሃይማኖት ሰውን ከፈጣሪው ጋር ሕብረት እንዲኖረው የሚያደርግ መሳሪያ ነው። ሃይማኖት ፀሐይን አቁሟል፣ ሰማይን ለጉሟል፣ እሳት አጥፍቷል ፣ የአንበሶችን አፍ ዘግቷል፣ ጠላትን ድል ነስቷል፣ ድንቅ ድንቅ ተአምራትን አድርጓል። የዚህ እውነት ምስክሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው።

ሃይማኖት ሰዎች ትልቅ ትንሽ ሳይባል በእግዚአብሔር የሚታዘዙበት የመታዘዝ ሕይወት ነው። ሃይማኖት ገንዘብ ያደረገ ሰው ለፈጣሪው ይገዛል። ሃይማኖት በሥጋ ኃይል የበረታውን መንፈሳዊነት የሚያደክም በጥበብ ሥጋዊ የበለፀጉ እና ያደጉ ሰዎች ወደ ጥበብ መንፈሳዊ የሚያሻግር ድልድይ ነው።
"የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሔደ በኢየሩሳሌም የደቀመዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ ከካህናትም ብዙዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ" ሐዋ 6:7

ሃይማኖት ብዙሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የሰበሰበ መረብ ነው። የሰበሰበም ብቻ ሳይሆን ያቀና ያጸናም ነው። ብዙዎችንም ለመከራ ያዘጋጀ ያስጨከነ ምድራዊ ክብር ትተው መንግስተ ሰማያትን ሽተው መከራ እንዲቀበሉ ያደረገ ነው።
" በዚያችም ከተማ ወንጌልን ሰብከው ብዙ ደቀመዛሙርትን ካደረጉ በኋላ የደቀ መዝሙሮችን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ፀንተው እንዲኖሩ እየመከሩ እና ወደ እግዚአብሔር መንግስት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ አለን እያሉ ወደ ልስጥራን ተመለሱ" ሐዋ 14: 21

ሃይማኖት የሰው ልጆች ራሳቸውን በቅድስና በንጽህና የሚያንጹበት እና የሚያነጹበት ነው። "ወይእዜኒ አሀዊነ ሕንጹ ርዕስክሙ በሃይማኖት ቅድስት ወመንፈስ ቅዱስ ጸልዩ " "አሁንም ወንድሞቼ ራሳችሁን በተቀደሰች ሃይማኖት እነጹ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ " ይሁ 20 የሰው ልጅ በተቀደሰች ሃይማኖት ራሱን እንደ ድውያንን የሚፈውስ የሃይማኖት ጸሎት ለፈጣሪው የሚያቀርብበት ነው። " ወጸሎተ ሃይማኖት የሐይዎ ለድውይ""በሃይማኖት የሚጸልዩት ጸሎት ድውዩን ያድነዋል" ያዕ 5:15

ሃይማኖት የሰው ልጆች ከታዘዘ መቅሰፍት ከዘላለም ሞት የሚድኑበት ተስፋ የሚያደርጓትን መንግስተ ሰማያትን የሚወርሱበት ነው።

"ዘዕቀብ ለነ ወለክሙ ለእለ በኃይለ እግዚአብሔር ዕቁባን በሃይማኖት ለመድሃኒት እንተ ድሉት ከመታስተርኢ በደኃሪ መዋዕል""በመጨረሻ ዘመን ይገለጥ ዘንድ የተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠመቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቆይቶላችኋል"1ጴጥ 1፡ 5

በሃይማኖት መከራ ተቀብለው ከወርቅ ከእንቁ የበለጠ ሰማያዊ ዋጋ የሚገኝበት ነው ዘላለማዊ ደስታን የሚያጎናጽፍ በክብር ላይ ክብርን የሚያሰጥ ነው።
"ወትትፌስሑ እስከ ለዓለም ወባህቱ ህዳጠ ይዕዜ ሀለወክሙ ትተክዙ በዘይመጽአክሙ መከራ ዘዚአሁ ከመ መከራ ለሃይማኖትክሙ ዘይትበደር ፈድፋደ እምነወርቅ ዘይማስን ዘበእሳት አመክርዎ ወትትረከብ ሀለዋ በክብር ወበውዳሴ ወበስብሐት ከመያስተርኢ ኢየሱስ ክርስቶስ" "በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር ሃይማኖታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋና ለክብር ለውዳሴ ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል"1ጴጥ 1፡9
ሃይማኖት የመልካም ሥራ መሰረት ነው ሰው በሃይማኖት ሲኖር መልካም መሥራት ግዴታው ነው "አትልውዋ ለሰናይት በሃይማኖትክሙ" "በሃይማኖት ላይ መልካም ሥራን ያዙ" 2ጴጥ 1፡5

በሃይማኖት መልካም ሥራን ማስከተል አስፈላጊ እንደሆነ ቅዱሳት መጻህፍት ያስረዳሉ "ምንት ይበቁእ አህዊነ ለእመቦ ዘይብል ሃይማኖት ብየ ወምግባረ ሠናይ አልቦ" "ሃይማኖት አለኝ የሚል ሰው መልካም ሥራ ግን የሌለው ሰው ምን ይጠቅማል" ያዕ 2፡14 በዚህ መሰረት ሃይማኖት የመልካም ሥራ የጾም የጸሎት የትሩፋተ ሥጋ የትሩፋተ ነፍስ መዲና ነው።

ሃይማኖት ከምግባር የማይለይ መልካም ሥራ ጌጡ ፈርጡ ሽልማቱ መለያው መታወቂያው ነው። ሃይማኖት ያለ ምግባር የሞተ ነፍስ የተለየው ነው፡ ከመልካም ምግባር ጋር ሰውን ፍጹም የሚያደርግ ሃይማኖት መልካም ተግባራት ከሌለው የአጋንንትን እምነት ይመስላል።
"ከማሁ ሃይማኖትኒ እንተ አልባቲ ምግባረ ሠናይ ምውት ይእቲ ለሊሃ እመቦ ዘይቤለከ እንተ ሃይማኖት ብከ ወአነ ምግባረ ሠናይ ብየ አርእየኒከ ሃይማኖተከ ዘእንበለ ምግባሪከ ወአነ አርእየከ እምነ ምግባርየ በሃይማኖትየ ወአንተሰ ተአምን ከመአሀዱ እግዚአብሔር ሰናየ ትገብር አጋንንትኒ የአምኑ ወይደነግጹ ትፈቅዱኑ ተአምር አ ብእሲ አብድ ከመሃይማኖት ዘእንበለ ምግባር ምውት ይእቲ" እንዲሁም ሥራ የሌለው ሃይማኖት በራሱ የሞተ ነው ነገር ግን አንድ ሰው እምነት አለህ እኔ ሥራ አለኝ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ እኔም እምነቴም በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካምም ታደርጋለህ አጋንንትም ያምናሉ ይደነግጣሉም አንተ ከንቱ ሰው ሃይማኖት ከሥራ ተለይቶ የሞተ እንደሆነ ልታውቅ ትወዳለህን? "
" አኮኑ አብርሃም አቡነ በምግባሩ ጸድቀ ሶበ አእረገ ለይስሐቅ ወልዱ ውስተ ምስዋዕ ትሬኢኑ ከመ ሃይማኖት ትረድአ ለገቢር ወበ ምግባሩ መልአተ ወፍጹመ ኮነት ሃይማኖቱ "" አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሰዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረም ? እምነት ከሥራ ጋር አብሮ ያደርግ እንደነበረ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን? " ያዕ 2፡14
ይህ የሚያሳየን ሃይማኖት በሥራ የሚገለጥ መሆኑን ነው።
ሃይማኖት ለሰው ይምሰል ሰውን ደስ ለማሰኘት የምንይዘው ሳይሆን ከፈጣሪያችን ጋር ለመገናኘት ነው።

"ወይእዜኒ አሀዊነ ኢትኩን ለገፀ ሰብእ ሃይማኖትክሙ እንተ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ" "ወንድሞቼ ሆይ በክብር ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ሃይማኖት ለሰው ፊት በማድላት አትያዙ" ያዕ 2፡1

ሃይማኖት የሰው ልጆች ዓለሙን የሚያሸንፉበት መሳሪያ ነው፡፡ ሰው በሃይማኖት ከእግዚአብሔር ተወልዶ ዓለም በውስጡ ያለው ፍላጎቱን ድል ነስቶ የሚኖርበት ነው፡፡

"እስመ ኩሉ ዘተወልደ እም እግዚአብሔር ይመውኦለ ዓለም ወዛቲ ይዕቲ ሙአቱ እንተ ሞኦ ለዓለም ሃይማኖትክሙ ""ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል የሚያሸንፈውም ይህ ነው ዓለምን የሚያሸንፈው ሃይማኖታችሁ ነው" 1ዮሐ 5፡4

ሃይማኖት እስከ ሞት የሚታመኑበት የሚጠብቁት እየሞቱ የሚኖሩለት እና የሚኖሩበት የክብር አክሊል የሚቀበሉበት ነው፡፡ በሚያልፍ በሚጠፋ ወርቅ ብር ቁሳቁስ አይተመንም

"ኩን መሀይምነ እስከ ለሞት ወእሁብከ አክሊለ ሕይወት" "እስከ ሞት የታመንክ ሁን የሕይወትን አክሊል እሰጥሀለሁ" ራዕ 2፡10 የኖሩበትን የጠበቁትን የሚያስከብር ሰማያዊ የክብር አክሊል መንግስተ ሰማያት የሚያወርስ ነው ሃይማኖት፡፡

"ወበጽሐኒ እድሜየ ለአዕርፎ ሰናየ ገድለ ተጋደልኩ በድርየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖትየኒ አቀብኩ እንከሰ ጽንሀ ሊተ አክሊለ ጽድቅ ዘየአስየኒ ይዕተ እለተ መኰንነ ጽድቅ""የምሄድበት ጊዜዬ ደርሷል መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቄያለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህን ጻድቅ እውነተኛ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም" 2ጢሞ 4፡5_8

## 1፡3 ሀልዎተ ፈጣሪ / የፈጣሪ መኖር

ሀልዎተ ፈጣሪ ማለት የፈጣሪ መኖር ማለት ነው፡፡ የፈጣሪ መኖር በሃይማኖት ለኖርን እና ለምንኖርም ሰዎች ድርድር ውስጥ የሚገባ ለውይይትም የሚቀርብ አይደለም፡፡ ሀልዎተ ፈጣሪ በብዙ መንገድ የታወቀ የተገለጠ ነው፡፡ ፈጣሪ ከሌለ ፍጡር ሊኖር አይችልም ሰሪ ሳይኖርም ሥራ ሊኖር አይችልም እና፡፡ ይህን ዓለም የወዲያኛውንም ዓለም የሚታየውን እና የማይታየውን ስውሩን እና ግልጡን ትንሹን ትልቁን በየብስ ያለውን በባህር ውስጥ የሚኖረውን በጠቅላላ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው፡፡ ከዘመናት በፊት የነበረ ዘመናትን ያስገኘ በዘመናት የሰለጠነ አምላክ ቅድመ ዓለም የነበረ በማእከለ ዘመን ያለ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር አምላክ መኖሩ ግልጽ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መኖር በልዩ ልዩ መንገድ ለፍጥረታት በፍጥረታት በመግቦት በመላእክት በነቢያት በሐዋርያት በሊቃውንት ተመስክሯል፡፡ አፍ ያለው መናገር የሚችል የሰው ልጅ በመጽሐፍ መናገር የማይችል ፍጡር ደግሞ በተግባር ሲመሰክረው የኖረ የነበረ እና የሚኖር ዘመን ያልሻረው ጊዜ ያልገደበው የዓለም ጥበብ እና ጠቢባን ያልሻሩት እውነት ነው፡፡

### <u>የፈጣሪ መኖር ምስክሮች</u>

**1. እራሱ እግዚአብሔር**

እግዚአብሔር የህልውናው ምስክር ነው፡፡ ቅድመ ዓለም ዘመን ያልተቆጠረለት ያለ ጊዜ እና ያለ ዘመን መኖሩን ለአበው ተናግሯል መስክሯል፡፡ መኖሩን የገለጠው ለደጋጎቹ ብቻ ሳይሆን ለክፉዎቹም መኖሩን

ገልጧል፤ “እግዚአብሔርም ቃየንን አለው ወንድምህ አቤል ወዴት ነው ? ” ዘፍ 4፡9 “ቃይንም እግዚአብሔርን አለው ኃጢያቴ ልሸከማት የማልችላት ከባድ ናት” ዘፍ4፡13 ከዚህ እንደምንረዳው ለተበደሉት የሚፈርድ እግዚአብሔር መኖሩን ለቃየን እንኳን ተገልጦ ነግሮታል። የፈጠረውን ፍጥረት የሚመግብ በፍጥረት ሁሉ የሰለጠነ ክፉውን ስለክፋቱ የሚወቅስ እንደሆነ ገልጧል። ለቃየን ራሱን የገለጠ እግዚአብሔር ራሱን ለኖኅ ገልጧል “እግዚአብሔርም ኖኅን አለው አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ በዚህ ትውልድ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ አግኝቼሀለሁ እና” ዘፍ6፡6 ፤ 7፡1

“እግዚአብሔርም ኖኅና ልጆቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት”ዘፍ9፡1 ይህን ያለ እግዚአብሔር መኖሩን ገልጧል ፡ አለሁ እያለ የለህም ማለት በጣም ጭፍንነት ነው።
“እግዚአብሔርም የሰው ልጆችን ከተማ ለማየት ወረደ ” ዘፍ11፡6 “እግዚአብሔርም አብራምን አለው ከዘመዶችህ ተለይ ከሀገርህ ውጣ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ ” ዘፍ12፡1

ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ቅዱስን ብናየው ለአበው ለክፉውም ለደጉም እግዚአብሔር መኖሩን በሰፊው ገልጧል። እግዚአብሔር ለፍጡራኑ ራሱን ከገለጠባቸው አንዱ መኖሩን የሚያሳይ ነው“አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ” “እኔ የአባቶችህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ እኔ ነኝ” ዘጸ 3፡6 “ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቷል እና ፊቱን ሸፈነ ግርማውን አይቷል እና ሙሴም እግዚአብሔርን እኔ ወደ እስራኤል ልጆች በመጣሁ ጊዜ የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልኩ ጊዜ የአባቶቻችህ አምላክ ስሙ ማን ነው ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ አለው እግዚአብሔርም ሙሴን ”ያለ እና የሚኖር“ ወደ እናንተ ላከኝ በላቸው አለው” ዘጸ3፡13_16

በእብራይስጥ ”አኽያ ሽራኽያ“ በግዕዝ "ዘሀሎ ወይሄሉ" በአማርኛ ”ያለ እና የሚኖር“ ይህን ለሙሴ የገለጠ ራሱ እግዚአብሔር እኔ አለሁ እያለ መስማትና ማየት ሲቻል የለም የለህም ማለት ስንፍና ነው “ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር” “ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል” “ብእሲ አብድ ኢየአምር ወዘ አልቦ ልብ ኢይሌብዎ ለዝንቱ” “ሰነፍ ሰው አያውቅም ልብ የሌለውም ይህንን አያስተውለውም” መዝ 13፡1 91፡6

“ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ ያለህ እና የነበርክ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ትልቁን ኃይልህን ስለያዝክ ስለ ነገሥክም እናመሰግንሃለን” ራዕ 11፡17 “የውሃውም መልአክ ያለህ እና የነበርክ ጌታ ሆይ ቅዱስ ሆይ እንዲህ ስለፈረድክ ጻድቅ ነህ” ራዕ 16፡5 “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረ እና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ይሰግዱ ነበር” ራዕ 4፡8 “ያለው እና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋ እና ኦሜጋ እኔ ነኝ” ራዕ 1፡8 እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው የመጻሕፍት ክፍሎች በሙሉ የእግዚአብሔርን ህልውና የሚመሰክሩ ናቸው። እግዚአብሔር መኖሩን የገለጠባቸው ዘላለማዊነቱን ያሳየባቸው ናቸው። እነዚህን መሰል ብዙ አሉ ብንጠቅሳቸው የሰማእያን ጆሮአቸው ይፈዝዛል አእምሮአቸው ይደነዝዛል የሚሻለን ህልውናውን አምነን መቀበል ነው።

2. የሰው ልጆች

ስለ ፈጣሪ መኖር ሰምተው ብቻ ሳይሆን አይተው የተናገሩ ሰዎች ብዙ ናቸው። ከደጋጎቹ አብርሐም

ፈጣሪውን አይቷል አብርሃም ብቻም ሳይሆን የሣራ አገልጋይ አጋርም ፈጣሪዋን አይታ መስክራለች "እርሷም ያናግራት የነበረውን የእግዚአብሔር ስም ኤልሮኢ ብላ ጠራች የሚያየኝን እዚህ ደግሞ አየሁት ብላለችና" ዘፍ 16፡13

በዓለም ጥበብ የተራቀቁት አወቅን ያሉት ሁሉ የዕውቀት ደረጃ ከአጋር በታች ነው እነርሱ ያላዩትን እርሷ አይታለችና እነርሱ ያልመሰከሩትን እውነት መስክራለችና፡ ማየት ሁሉ የሚያከትምበትን ፈጣሪዋን አይታ መስክራለችና "ዘበ ኀሀቤከ የአርፍ ነጽሮተ ኵሎሙ ነባቢያን" "ማየት የሚችሉ የሰዎች እይታ ሁሉ ባንተ ያልቃል" አረጋዊ መንፈሳዊ

ሰው አዲስ ነገር ማየት ይወዳል ሲያየው ያረጅበታል ሌላ ይፈልጋል እግዚአብሔርን ከማየት በኋላ ግን ሌላ አዲስ እይታ የለም የማያረጅ የማይጠገብ ልዩ እይታ ነው "ዘያፈትዎሙ ለመላዕክት ከመ የሐውፅዎ " "ያዩት ዘንድ መላዕክትን የሚያስመኛቸው" 1ጴጥ ያዩታል አይሰለቹትም፤ መጽሐፈ ኪዳን፡፡ያዩት መላዕክት ይመሰክራሉ አጋርም ለዚህ ምስክርነት የበቃች ናት፡፡

"ወእምዝ በዓመተ ሞተ ኦዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ዲበ መንበሩ ነዋህ ወብሩህ ""ንጉሡ ኦዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁት የልብሱም ጫፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር" ኢሳ 6፡1 ኢሳይያስ የመሰከረው አይቶ ነው እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥለት ለወደደው ሰው ሁሉ ገልጧል፡፡ "ጌታን በመሰዊያው አጠገብ ቆሞ አየሁት " አሞ 9፡1 ዳዊትም ስለ እርሱ እንዲህ ይላል "ጌታን ሁል ጊዜ በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም" መዝ 15፡8

ነቢያት በልዩ ልዩ ህብረ አምሳል አይተውት መስክረዋል ፤ ሙሴ በአምሳለ ነበልባል ዳንኤል በአምሳለ አንበሳ ሌሎቹም ነቢያት አይተው መስክረውለታል፡፡ ይህንን እውነት አምኖ መቀበል የሰው ድርሻ ነው፡፡ እኔ ካላየሁት የለም ልንለው አንችልም፡፡ ሰው ቅንድቡን በመስታወት ካልሆነ አያየውም አላየሁትምና የለም ሊል አይችልም፡ ማንም ሰው ነፍስ አለችው አይቷት አያውቅም መኖሯን ግን ተጠራጥሮ አያውቅም፡፡ ማንም ፍጡር በውስጡ አይቷቸው የማያውቅ የሰውነት ክፍሎች በእጁም በእግሩም ውስጥ ብዙ ስሮች እንዳሉት ያምናል ካላየኋቸው አላምንም ብሎ አያውቅም መኖራቸውን አምኖ ይኖራል፡፡ እግዚአብሔርን ካላየሁት የለም ፡ አላምንም ልንለው አንችልም፡፡ ይልቁንስ መጻሕፍትን ተመልክተን የአበውን ዓይን ዓይን አድርገን አምነን ተቀብለን መኖሩ ያዋጣናል፡፡ ካላየሁ አላምንም ማለት አያስመሰግንምና ፡፡ ቶማስ ካላየሁ አላምንም ማለቱ አላስመሰገነውም አይቶ አምኖ "እግዚእየ ወአምላኪየ" "ጌታዬ አምላኬ" ሲል "ስላየህ አመንክ ብፁዓንስ ሳያዩ የሚያምኑ ናቸው" ዮሐ 20፡ 29

## 3 ሥነ_ፍጥረት እና መግቦቱ

እግዚአብሔር መኖሩን የገለጠበት የፈጣሪ መኖር የታወቀበት ፍጥረቱ መግቦቱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ተቆጥሮ ተሰፍሮ የማያልቅ ፍጥረትን ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ አንዱን በአንዱ እየመገበ ዓለምን ያስተዳድረዋል፡፡ ሰማይን ምድርን ያህል ግዙፍ ፍጥረት ፈጥሮ ቀን ብርሃንን ያጎናጽፈዋል ሌሊት ሌሊት በጨለማ ይሸፍነዋል፡፡ ሰውን ያህል ፍጥረት ፈጥሮ በምድር አስፍሮ የምድርን በረከት መግቦ ያኖረዋል፡ እንስሳትን ፈጥሮ ግማሹን ለምግበ ሥጋ እና ለአንክሮተ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ በውሃ እና በሳር እየመገበ እያጠገበ ያኖረዋል፡፡ መሬቱን በእጽዋት ይሸፍነዋል፡ እጽዋት አትክልትን አፈር አብልቶ ውሃ አጠጥቶ እያለመለመ፡ ሰውና

እንስሳትንም ከተገኙበት የሥጋ ባህርይ የበቀለውን እጽዋት አትክልት መግቦ አጥግቦ ከእጽዋት የሚገኘውን አየር ስቦ እንዲኖር ያደርገዋል። ሰፊውን ምድር በእጽዋት ሰፊውን ሰማይ በከዋክብት በፀሐይ በጨረቃ ያስጌጠዋል፡ ክረምቱን በጊዜው በጋውንም በሰዓቱ ያመጣዋል። ይህ መግቦቱ የፈጣሪ መኖር ምስክር ነው። ይህ ያለፈጣሪ ያለ መጋቢ ይሆናል ብሎ የሚታሰብ አይደለም። ተፈጥሮ ሰዓቱን እና ሚዛን ጠብቆ ስፍራውን እና ሥራውን አውቆ የሚኖረው ሰው በማይገነዘበው የአምላክ ድንቅ ጥበብ ነው። ውቅያኖስን በሥፍራው የወሰነው እርሱ ነው። ሰውን በቀን አራዊትን በሌሊት የወሰነ የውቅያኖስን ዳርቻዎች የመጠነ እርሱ ነው። ፀሐይን በቀን ጨረቃን ከዋክብትን በሌሊት ያሰለጠነ እርሱ ነው። እንኳን ይህ ሁሉ ፍጥረት በዓለማችን ሰው የሰራቸው ቁሳቁሶች ባለቤት አላቸው።"በምድር ዳርቻ ሁሉ እና በሩቅ ባህር ውስጥ ላሉት ተስፋቸው የሆንክ አምላካችን እና መድሃኒታችን ሆይ ስማን በጉልበትህ / በኃይልህ ተራሮችን አጸናሃቸው በኃይልህም ታጥቀዋል፡ የባህሩን ጥልቀት የሞገዱንም ጩኸት ታናውጣለህ ከተአምራትህ የተነሳ አሕዛብ ይደነግጣሉ" መዝ 64፡5_13 "ወሰኖሙ᎓ ኢም ሀበ ኢየሀልፉ ከመ ኢይትመየጡ ወኢይክድንዋ ለምድር " "እንዳያልፉ ድንበር አደረግክላቸው ምድርን ይከድኑ ዘንድ እንዳይመለሱ፡ ምንጮችን ወደ ቆላዎች ይልካል በተራሮች መካከል ውሆች ያልፋሉ የዱር አራዊትን ሁሉ ያጠጣሉ የበረሀ አህዮችም ጥማታቸውን ይረካሉ የሰማይ ወፎችም በነርሱ ዘንድ ያድራሉ" መዝ103፡ 5_35 በዚህ ሥራው እግዚአብሔር መኖሩ ይታወቃል። እነዚህ ሁሉ መኖሩን በኑሮ ይመሰክራሉ። "ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር ወግብረ እደዊሁ ያየድአ ሰማያት" "የእጆቹ ሥራ የሆኑ ሰማያትም የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ይመሰክራሉ" መዝ 18፡1 "ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትአወቅ ለፍጥረቱ በህልዮ ወበ አእምሮ ወከመዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም" "ከዓለም መፈጠር በፊት የማይታይ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይታወቃል ኃይሉ የዘላለም ጌትነቱም እንዲህ ይታወቃል" ሮሜ 1፡21_23 ከዚህ አንጻር የእግዚአብሔርን ህልውና ለማወቅ ሥነ_ፍጥረትን ማየት አስፈላጊነው የህልውናው መገለጫዎች ናቸውና። "ወእንዘ ኢየሀድግ ርዕሶ ዘእንበለ ሰማዕት " "ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሰራ ከሰማይ ዝናምን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን ልባችንንም በመብል እና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም" ሐዋ 14፡17

## 1.4 የሥነ_ፍጥረት ምንነት

እግዚአብሔር ህልውናውን ከገለጠባቸው መንገዶች ትልቁን ስፍራ ይዞ የሚገኘው ሥነ_ፍጥረት ነው። እግዚአብሔር ሥነ_ፍጥረትን በየወገኑ ፈጥሯል፡ ቅድመ ዓለም እግዚአብሔር ምሥጋናን ከማንም ሳይሻ ያልተቆጠሩ ያልተሰፈሩ ዘመናትን ኖሯል፡ "እምቅድመ ይፍጥር መላዕክተ ለቅዳሴ አኮ ዘተጸርአ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ ወውዳሴሁ እምዚአሁ" "መላዕክትን ለምሥጋና ሳይፈጥር የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ምሥጋና አልተቋረጠም ምሥጋና የራሱ ገንዘቡ ነውና" ዮሐንስ አፈወርቅ።

ዘመን እንዲቆጠር እንዲሰፈር በዘመናት የሚኖሩ ፍጥረታት ክብሩን እንዲወርሱ ስሙን እንዲቀድሱ መላዕክትንና ሰውን ፤ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ እንስሳት አራዊትን እፀዋት አዝርዕት አትክልትን ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብትን ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ፈጠረ ። በተጨማሪም ለአንክሮ ለተዘክሮ ፈጠረ። ይህም ክብሩ ይገለጥ መግቦቱ ይታወቅ ይመሰገንበትም ዘንድ ነው "እስመ በኩሉ ይሴባሕ እግዚአብሔር" "እግዚአብሔር በሁሉ ይመሰገናልና " ቅዱስ ያሬድ። "ወለኩሎሙ እለ ተፈጥሩ ለስብሐትየ ፈጠርክዎሙ ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተገብሮ ""የተፈጠሩትን ሁሉ ጌትነቴ ይገለጥ ይታወቅ ዘንድ ፈጠርኳቸው ከእነርሱ

ለትምህርት የሚሆን አለ ለተግባረ ሥጋ የሚሆን አለ" "አንተ ሰነፍ ወደ ግብረ ጉንዳን ተመልከት" እንዲል ምሳ 6፡6 ፡፡

ከነዚህ ፍጥረታት በየብስ የሚኖር አለ በባህር ውስጥ የሚቀመጥ አለ ግማሹ በምድር የሚመላለስ ከፊሉ በባህር የሚንቀሳቀስ ግማሹ በክንፍ የሚበር ከፊሉ በምድር የሚሽከረከር የተወሰነው በደረቱ የሚሳብ ከፊሉ በእግሩ የሚያኮበኩብ አለ፡፡ እነዚህ ሁሉ ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚመሩ ለእግዚአብሔርም የሚመሰክሩ ናቸው፡፡ "ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘንተ ብከ ሰማዕት ወመምህር እምአፍአ ዘይመርሀሁ ለልብከ ኀበ አእምሮተ እግዚአብሔር ከመ ትኩን ፍቱነ ወስቡከ ""ይህን ልታውቅ ከወደድክ የተማርክ እና የተፈተንክ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔርን ወደማወቅ የሚያደርስ ሥነ _ፍጥረት አለልህ"እንዲል ማርይስሐቅ፡፡

እግዚአብሔር ሥነ_ፍጥረትን አምስት ነገሮች ለማስረዳት ፈጥሮታል፤

1. ከኃሊነቱን (ችሎታውን)
2. ባዕልነቱን (ባዕለ ፀጋነቱን)
3. ርኩብነቱን (ለሚሹት የሚገኝ መሆኑን)
4. ዘኢይትረከብነቱን (ለማይፈልጉት የማይገኝ መሆኑን)
5. ራትዕነቱን (ፍርዱ የቀና መሆኑን)

**1ኛ. ከኃሊነት**

ከኃሊነት ማለት ሁሉን ቻይነት ገንዘቡ እንደሆነ ያስተምረን ዘንድ ነው፡፡ ይህም የሚታወቀው ይህን ዓለም "እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ" " ካለመኖር ወደ መኖር" አምጥቶ በመፍጠሩ ነው፡ ኋላም "እም ኀበ ቦ ኀበ አልቦ""ከመኖር ወዳለመኖር በማሳለፉ ነው" "ወኵሉ ከመ ልብስ ይበሊ ወከመ ሞጣህት ትዌልጦ ወይትዌለጡ አንተሰ አንተ ክመ ወዓመቲከኒ ዘኢየሀልቅ" "ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል እንደ መጋረጃ ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል አንተ ግን መቼም መች አንተ ነህ ዘመናትህም አያልፉም" መዝ 103፡26
"ሰማይ ወምድር የሀልፍ ወቃልየሰ ኢየሀልፍ" "ሰማይ እና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም" ማቴ 24፡35 ይህን በማድረጉ ከኃሊነቱ ይታወቃል፡፡ ከዚህ የተነሳ ኤልሻዳይ ይባላል፡፡ በግዕዝ ከኃሌ ኩሉ፡፡ በአማርኛ ሁሉን ቻይ ማለት ነው፡፡"ይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ" "ሁሉን ይችላል የሚሳነው የለም" አባ ጊዮርጊስ ፡ "እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር" "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" ሉቃ 1፡37

**2ኛ. ባዕለ ፀጋነት**

ባዕለ ፀጋ ብዙ ሰው ጠርቶ ሥጋ ላለው ሥጋ ጠጅ ላለው ጠጅ ሰጥቶ እንዲያጠግብ እርሱም እንስሳት አራዊትን ሰውን ፈጥሮ ግዙፍ ምግብ አዝርዕት አትክልት … በመመገቡ፤ ረቂቃን ፍጥረታት ነፍሳትን መላዕክትን ፈጥሮ ረቂቅ ምግብ ውዳሴ ቅዳሴ ምሥጋና ተመግበው እንዲኖሩ በማድረጉ ባዕለ ፀጋነቱ ይታወቃል፡፡ "ምግባቸውን ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ በሰጠሀቸውም ጊዜ ይሰበስባሉ እጅህን ትከፍታለህ ከመልካም ነገር ይጠግባሉ ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ ነፍሳቸውን ታወጣለህ ይሞታሉ" መዝ 103፡27 "እስመ ባዕል እግዚአብሔር ወየአክል ለኩሉ" "እግዚአብሔር ባዕለ ፀጋ ነውና

ለሁሉ ይበቃል" እንዲል መጽሐፍ

3ኛ. ርኩብነት

ርኩብነት ማለት ለሚፈልጉት የሚገኝ መሆኑ በሥነ _ፍጥረቱ ይታወቃል። "ዓለም ሳይፈጠር አይታይ የነበረው እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል" ሮሜ1፡22_23 ይኸውም አብርሃም፡ ሙሴ ጳሊም ፡ አባ ማቴዎስ በሥነ_ፍጥረት ተመራምረው ፈልገውት እግዚአብሔርን አግኝተውታል። ሥነ_ፍጥረትን ተመልክተው የፈለጉት ሁሉ አግኝተውታል ። ርኩብነቱ ይህን የሚያስረዳ ነው። "ወረከብናሁ ውስተ ገመ ገዳም" "በዱር ውስጥ አገኘነው" መዝ 131፡6 "ረከብናሁ ለኢየሱስ ወልደ ዮሴፍ ዘእምናዝሬት ዘጸሐፈ ሙሴ ውስተ ኦሪት ወነቢያት ተነበዩ በእንቲአሁ" "ሙሴ በኦሪት የጻፈለትን ነቢያት ትንቢት የተ ናገሩለትን አይሁድ ወልደ ዮሴፍ የሚሉትን የናዝሬቱን ኢየሱስን አገኘነው" ዮሐ 1፡46

4ኛ. ዘኢይትረከብነቱ

ዘኢይትረከብ (የማይገኝ ) መሆኑ፡ በቅን ልቡና በትሁት ስብእና ሆነው ለማይፈልጉት የማይገኝ መሆኑን ለማስተማር፡ ለሚፈልጉት ቅርብ ለማይፈልጉት ሩቅ መሆኑን ለማስረዳት "ቅሩብ እግዚአብሔር ለየዋሀነ ልብ ወያድኅኖሙ ለትሁታነ መንፈስ" "እግዚአብሔር ቅን ልቡና ላላቸው ቅርብ ነው መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል"መዝ 33፡18 "" "ቅረብዎ ለእግዚአብሔር ወይቀርበክሙ" "እግዚአብሔርን ቅረቡት ይቀርባችኋል" ያዕ 4፡8 እነዚህ ሁሉ ለሚፈልጉት የሚገኝ ለሚቀርቡት የሚቀርብ ለማይቀርቡት ሩቅ እንደሆነ ያስረዳሉ። "ተሐሥሡኒ ወኢትረክቡኒ ወኀበ አነ አሀውር አንትሙ ኢትክሉ መጺአ" "ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝም እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም" ዮሐ 8፡21 በዘፍጥረት ፈልጎታልና እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጧል ዘፍ18፡1፤ ያዕቆብ በዘፍ 28፡13 ፤ "ሀሰስክዎ ወኢረከብክዎ ፀዋዕክዎ ወኢተሰጥወኒ" "ፈለግኩት አላገኘሁትም ጠራሁት አልመለሰልኝም" መኃ 5፡6። እነዚህ ከላይ ያየናቸው ለሚፈልጉት የሚገኝ ለማይፈልጉት የማይገን መሆኑን ያስረዳሉ።

5ኛ. ራትዕነት

ራትዕነት (ቅን ፈራጅ መሆኑ ) ቅን ፈራጅነቱ በአዳም እና በዲያቢሎስ ታውቋል፡ ዲያቢሎስ ሲወድቅ እንዳይመለስ ያውቃልና ቦታውን ለሌላ አሳልፎ ሰጥቶበታል። አዳም ሲስት በንስሐ እንደሚመለስ ያውቃልና ቦታውን ለሌላ አልሰጠበትም፡ ይልቁንም በመላዕክት አስጠበቀለት ዘፍ 3፡24 ። ይህን ያስረዳን ዘንድ ፍጥረትን ፈጠረ፡ አከናወነ ። "እግዚአብሔር መኮንነ ጽድቅ" "እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ነው" መዝ7፡12

ፍጥረትን ከአራቱ ባህርያት (ከውሃ ከነፋስ ከእሳት ከመሬት) ፈጠረ ፡ በባሕርዩ አራት ነገሮች እንዳሉ ለማስረዳት።

1ኛ .ኃያልነት

2ኛ .ፈታሂነት

3ኛ. መንጽሂነት

4ኛ_ባዕልነት

**1ኛ እሳትነት** _ እሳት ኃያል ነው ባህር ገደል ካልከለከለው ሁሉን ያጠፋልና ፡ እግዚአብሔርም ትዕግስቱ ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ሳጥፋ ቢል ይቻለዋል "እግዚአብሔር ኃያል ወመስተአግሥ" "እግዚአብሔር ኃይለኛ እና ታጋሽ ነው" መዝ7፡12። ኃያልነቱን ለመግለጽ እሳትን ፈጠረ።

**2ኛ ነፋስነት_** ነፋስ ገለባውን ከፍሬ ፍሬውን ከገለባ ይለያል። እግዚአብሔርም ጻድቃንን ከኃጥአን ፡ ኃጥኡን ከጻድቁ አማኒውን ከመናፍቁ ይለያልና። "ወያቀውም አባግዐ በየማኑ ወአጣሌ በጸጋሙ" "በጎችን በቀኝ ፍየሎችን በግራ ያቆማል"ማቴ 25፡36

**3ኛ *መንጽሂነት*_**ውሃ ያነጻል ያጥባል ያጠራል፡ ጌታም መንጽሄ ሥጋ ወነፍስ ነውና። ሥጋን ከኃጢአት ያነጻልና ውሃን ፈጠረ። ውሃ የደረቀውን ያለመልማል የለመለመዉን ፍሬ እንዲሰጥ ያደርጋል፡ ጌታም ምዕመናንን ፍሬ ትሩፋትን ፍሬ ክብርን እንዲያፈሩ ያደርጋልና። "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይችል እንዲሁም እናንተም በእኔ ባትኖሩ አትችሉም" ዮሐ 15፡4 ።

**4ኛ ባዕልነት**__ባዕለ ፀጋ መሆኑን ለማስረዳት መሬትን ፈጠረ። መሬት ለፍጥረት ሁሉ ምግብን ታስገኛለች "ወበረከተ ምድር እንተ ኩሉ ባቲ" "ሁሉ ያላት የበረከት ምድር እንዲል" መጽሐፍ እግዚአብሔርም ሁሉን ይመግባልና። በዚህ መልኩ ሥነ_ፍጥረትን የፈጠረው የርሱን ኃያልነት ፈታሂነት መንፅሂነት ባዕልነት እንማርበት ዘንድ ነው። በሚታይ በሚዳሰስ ጉልህ በሆነ ያስተምረን ዘንድ ስለፈለገ ፍጥረትን አዘጋጀ ከአራቱ ባህርያት አንድ ፍጥረት ፈጥሮ የማይስማሙትን ነፋስንና መሬትን ውሃ እና እሳትን አስማምቶ አንድ መሆን የማይችሉትን አንድ ማድረግ የሚቻለው ኃያል መሆኑን ያሳያል። በዚህ መሰረት አምላካችን ብዙውን አንድ እያሉ ቢቆጥሩት ከእሁድ እስከ ዓርብ ሃያ ሁለት ፍጥረታትን ፈጥሯል።

**እሁድ**

ነፋስ፣እሳት ፣ውሃ ፣መሬት ፣ብሩህ ሰማይ ጽልመት፣መላእክት= 7

**ሰኞ**

ጠፈር = 1

**ማክሰኞ**

አዝርዕት፣አትክልት፣ዕፀዋት፣ዕፀወ ገነት = 4

**ረቡዕ**

ጨረቃ፣ ፀሐይ ፣ከዋክብት = 3

**ሐሙስ**

እንስሣት ፣አራዊት፣ አዕዋፍ = 3

**ዓርብ**

እንስሣት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ፣ አዳም = 4

በጠቅላላ በሰንጠረዡ የተዘረዘሩትን 22 ይሆናሉ፡፡

<u>በእለተ እሁድ</u> ፡ *ሥነ ፍጥረት ላይ ብርሃንን 8ኛ አድርገው የሚቆጥሩ አሉ፡ ከላይ ባየነው ብርሃን ከእሳት ጋር አብሮ ስላለ ራሱን ችሎ አይቆጠርም፡፡ በጠቅላላው በዕለተ እሁድ 7 ፍጥረታትን ነው አምላካችን የፈጠረው፡፡ ብርሃንን ከተዳፈነ እሳት በጭድ እንደ ማያያዝ መግለጥ ነው፡ ለዚህም የሚከተለው የመጽሐፍ ክፍል ማስረጃ ነው "ወገብረ እግዚአብሔር በቀዳሚት እለት ሰብዓተ ዘመደ ዐበይተ" "በመጀመሪያው ቀን ሰባት ታላላቆች ፍጥረታትን ፈጥሯል እና"* ኩፋሌ 2፡8

<u>ሰኞ</u> *የተፈጠረው አንድ ነው ፡ ይኸውም ጠፈር የሚባለው የብርሃናት መመላለሻ ነው፡"በሁለተኛው ቀን በሀኖስ እና በውቅያኖስ መካከል ጠፈርን ፈጥሯልና"* ኩፋሌ 2፡9

<u>ማክሰኞ</u> በሰንጠረዡ የተዘረዘሩትን *አራቱን ፍጥረታት ፈጥሯል፡ "በየዘሩ የሚዘራውን ዘር ፡የሚበላውንም ዘር ሁሉ የሚያፈሩትንም እንጨቶች ዛፎችንም በገነት ለተድላ ደስታ የተፈጠሩ ተክሎችንም በሦስተኛይቱ ቀን እነዚህን አራቱን ታላላቅ ፍጥረታት ፈጠረ"* ኩፋሌ 2፡10_13

<u>ረቡዕ</u> ፡ *"በአራተኛይቱም ቀን ጨረቃን ፀሐይን ከዋክብትን ፈጥሮ በዓለም ሁሉ ያበሩ ዘንድ በጠፈር አኖራቸው ሌሊት እና ቀንንም አስገዛቸው በጨለማ በብርሃን መካከልም ለመለየት ድንበር አደረጋቸው በአራተኛዪቱም ቀን እነዚህን ሦስቱን ፍጥረቶች ፈጠረ"* ኩፋሌ 2፡13_14

<u>ሐሙስ</u> ፡ *" በአምስተኛዪቱም ቀን በጥልቅ ውሃ ውስጥ መካከል ያሉትን ታላላቆች አንበሪዎችን ፈጠረ የሁሉ መጀመሪያ በስልጣኑ ተፈጥሯልና ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ በውሃዎች ውስጥ የሚመላለስ ፍጥረት ሁሉ የሚበርሩ ወፎች አሳዎችም ወገኖቻቸውም ሁሉ ተፈጥረዋልና ... በአምስተኛዪቱ ቀን እነዚህን ሦስቱን ፍጥረታት ፈጠረ"* ኩፋሌ 2፡15

<u>ዓርብ</u>*"በስድስተኛዪቱ ቀን እንስሳትን እና አራዊትን ሁሉ በምድርም ላይ የሚመላለሱትን ፍጥረት ሁሉ ፈጠረ "*ኩፋሌ 2፡17 *"ይህን ሁሉ ፍጥረት ከፈጠረ በኋላ አንድ ሰውን ፈጠረ ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው በባህር ውስጥ ባለው ፍጥረት እና በምድር ላይ በሚመላለሰው ፍጥረት ሁሉ አሰለጠናቸው በአራዊት እና በአእዋፍም ላይ በዚህም ዓለም በሚመላለሰው ፍጥረት ሁሉ በዚህ ሁሉ አሰለጠነው በስድስተኛዪቱ ቀን እነዚህን አራቱን ፍጥረቶች ፈጠረ የተፈጠረውም ፍጥረት ሁሉ 22 ፍጥረት ሆነ በስድስተኛዪቱ ቀን በምድር እና በሰማይ በጥልቁ እና በባህሩ ውስጥ በጨለማ እና በብርሃን መካከል በዓለምም ላይ ያለውን ሥነ_ፍጥረት ሁሉ ፈጥሮ ጨረሰ"* ኩፋሌ 3፡1_3

*ሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት የሚባለው ይህ ነው ከዚህ መጨመርም መቀነስም አይቻልም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ጥልቅ ትምህርት አለ፡፡*

በእለተ እሁድ አስራወ ፍጥረታት የሚሆኑ አራቱ ባህርያት ተገኝተዋል፡፡ በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ትምህርት እለቱ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን "ለዘኮነ ምክንያተ ሕይወት በህላዌሁ" የተባለ ጌታ ከርሷ ተገኝቷልና፡፡ በመኖሩ የሕይወታት አስገኝ የሚሆን ከሦስቱ አካላት አንዱ ቃል ከእመቤታችን አራቱን

ባህርያተ ሥጋ አምስተኛ ባህርየ ነፍስን ነስቶ ሰው ሆኗልና ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት እንዲሆን ሰው ሆኖልናል በዚህ ነገረ ሥጋዌን እንማርበታለን።

<u>በዕለተ ሰኑይ ፡</u> "ለይኩን ጠፈር" ባለ ጊዜ የብርሃናት መመላለሻ የሚሆን ጠፈር ተገኝቷል፡ እለት የእመቤታችን ጠፈር ከርሷ የነሳው ሥጋ ብርሃን የጌታ ምሳሌ ነው። ጌታም ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ሰው ሆኗልና ።

<u>በዕለተ ሠሉስ</u>፡"ለታብቁል ምድር ሐመልማለ ዘርዕ" ባለ ጊዜ "ዘር የሚገኝበትን ቡቃያ ታብቅል" ብሎ ሲናገር ለሥጋውያን ምግብ የሚሆኑ በጥፍር የሚጠቀሙ አትክልት በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት በምሳር የሚቆረጡ እፀዋት ተገኝተዋል። ከእመቤታችንም የመንፈሳውያን ምግብ የሚሆን ፍሬ ሕይወት እፀ መድሃኒት ጉንደ ሐረገ ወይን ክርስቶስ ተወልዷልና።

<u>በዕለተ ረቡዕ፡</u> "ብርሃናት በጠፈር ላይ ይሁኑ " ባለ ጊዜ ለሥጋውያን ምግብ የሚሆኑ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ተገኝተዋል፡ ከእመቤታችንም ፀሐየ ጽድቅ ኮከበ ብርሃን የሚባል ጌታ ተወልዷልና።

<u>በዕለተ ሐሙስ፡</u> በልብ የሚሳቡ በእግር የሚሽከረከሩ በክንፍ የሚበሩ ፍጥረታት ተገኝተዋል፡ እለት የእመቤታችን ባህር የጥምቀት ምሳሌ፡ ከእነዚህ እለቱን ወጥተው በርረው በርረው የሄዱ አሉ፡ ከዚያው የቀሩም አሉ፡ ወጥተው በርረው በርረው የሄዱት የኢጥሙቃን ፡ ከዚያው የቀሩ የጥሙቃን ምሳሌዎች ናቸው። በሌላ መልኩ በልብ የሚሳቡ የሰብዓ ዓለም በእግር የሚሽከረከሩ የባህታውያን በክንፍ የሚበሩ ተመስጦተ ጸጋ ያላቸው ከገድል ወደ ገድል የሚሉ የሰማዕታት ምሳሌዎች ናቸው። በአኗኗራቸው ከባህር ውለው ከዚያው የሚያድሩ አሉ፡ አንድ ጊዜ ወደ የብስ አንድ ጊዜ ወደ ባህር የሚሉ አሉ ፡ እነዚህ በገዳም መከራ ሲጸናባቸው ወደ ዓለም፡ ዓለም ሲሰለቻቸው ወደ ገዳም የሚሉ የነ ገብቶ ወጥ ምሳሌ ናቸው። በዚያው ጸንተው የሚኖሩት ደግሞ ዓለምን ንቀው በአት አጽንተው የሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ ነው።

<u>በዕለተ ዓርብ</u>፡ የፍጥረታት ሁሉ ጌታ አዳም ተፈጥሯል። ከእመቤታችንም ዳግማይ አዳም የሚባል ጌታ ተወልዷልና።

በጠቅላላው በስድስቱ ቀን ከተፈጠሩት ሥነ_ፍጥረታት ምስጢረ ሥላሴን ምስጢረ ሥጋዌን ምስጢረ ጥምቀትን ምስጢረ ቁርባንን ምስጢረ ትንሣኤ ሙታንን እንማርባቸዋለን።

ይህንን ሥነ_ፍጥረት አስገኚው እግዚአብሔር መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። አንዳንዱ መጻሕፍት በጅምላና በዝርዝር አልያም እንደሸማ ጠቅልሎ እንደወርቅ አንከብልሎ "ሁሉን የፈጠረ" በሚል አገላለጥ የሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ያስረዳሉ። ነቢያት ሐዋርያት ሊቃውንት በሰፊው ከገለጡት ጥቂቶቹን ለማስረጃነት እንመልከት፡

"በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ " "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" ዘፍ 1፡1 ሰማይ በማለት በሰማይ ያሉትን ምድር በማለት በምድር ያሉትን አንድ ላይ ጠቅልሎ ተናግሯል ነቢዩ ሙሴ።

"እግዚአብሔር ሁሉን ለርሱ ለራሱ ፈጠረ ኀጥአንን ደግሞ ለክፉ ቀን" ምሣ 16፡4

"ሰማያትን የፈጠረ  የዘረጋቸውም ምድርንና በውስጧ  ያለውን ያጸና " ኢሳ 42፡5 "ምድርን በኃይሉ የፈጠረ ሰማያትንም በጥበቡ ያጸና የመሰረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው" ኤር 51፡15

"እነሆ  ተራሮችን የሰራ ንፋስንም የፈጠረ " አሞጽ 4፡13
"ከዚህ ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን ባህርንም በርሷም ያለውን ሁሉ ወደፈጠረ ወደ እግዚአብሔር ትሉ ዘንድ ወንጌልን እንሰብካለን" ሐዋ 14፡15

ጠቅላላውን መጻሕፍቱ የሚነግሩን ይህን መሰል ነገር ሰፊ ነውና መጻሕፍቱን አገላብጠን ማንበብ ለዚህ ጠቃሚ ነው "ስህትክሙ በኢያእምሮ መጻሕፍት ወኢ ኃይለ እግዚአብሔር"

## 1.5 የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮች

**1ኛ .ሀልዎተ እግዚአብሔር**
"የእግዚአብሔር መኖር " ዋናው የሃይማኖት ምንጭ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ለልዩ ልዩ ሰዎች መግለጡ ድንቅ ሥራዎችን ሰርቶ ሰዎችን በሀብት መሳቡ በረድኤት ማቅረቡ ሰዎች እንዲያምኑበት የሃይማኖትን መንፈስ በውስጣቸው ማሳደሩ "ወብነ መንፈስ ዘሃይማኖት" "የሃይማኖት መንፈስ አለን" እንዲል መጽሐፍ ። ማመን መቀበል የሚችል ልብ ሰጥቶ በውስጣችን እምነት ሲጎድል እየሞላ ነገረ ሃይማኖትን የገለጠ ራሱ ባለቤቱ ነው። ምክንያትም ሃይማኖትን ለቅዱሳን አበው የሰጠ ትምህርቱንም ለአበው የገለጠ ነቢያትን በትንቢት ያጸና ልቡናችንን በሃይማኖት ያቀና እርሱ ነው። በዚህም መሰረት የነገረ ሃይማኖት መሰረቱ ሀልዎተ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ከሌለ ፍጥረት የለም፡ ፍጥረት ከሌለ ሃይማኖት ነገረ ሃይማኖት አይኖርም። ምክንያቱም ሃይማኖት ሰው እና እግዚአብሔር የሚገናኙበት ነውና፡ ነቢያት ለተልእኮ ከመላካቸው መጻሕፍትንም ከመጻፋቸው በፊት ሰዉን በሕገ ልቡና  ፈጥሮ እምነት በልቡናው አሳድሮ መስዋየሚዕት እንዲሰዋለት ምሥጋና እንዲያቀርብለት ያደረገው እርሱ ነው። "በተአምኖ ሀየሰ መሥዋዕተ አቤል እምዘቃየን" "አቤል በእምነት ከቃየን የሚበልጥ መሥዋዕት አቀረበ" ዕብ 11፡3። ይህ የሚያሳየን ነቢያት ሳያስተምሩት ሕግ ሳይሰራለት መጻሕፍት ሳይጻፉለት እግዚአብሔርን አምኖ መሥዋዕት ማቅረቡ የሃይማኖት ምንጨ ሀልዎተ እግዚአብሔር መሆኑን ያስረዳል።

**2ኛ ስብከተ ነቢያትነቢያት** ከእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ከፈጣሪያቸው ጋር ቃል በቃል ተነጋግረው ሰውን ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲመለስ ከሕገ ጣኦት እንዲፈልስ አስተምረዋል የነገራቸውም መነሻ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚል ነበር ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ እንዲያመልክ የሚያደርግ ነበር። የነቢያት ዋና ተግባር የእግዚአብሔርን መኖር ለሕዝቡ መግለጥ እና ድንቅ ሥራውን መመስከር ቀድሞ ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች መመስከር ቀድሞ ያደረጋቸውን ወደፊትም የሚያደርጋቸውን መናገር ነበር። እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ ነቢያት ሳይገልጠው የቀረ ምሥጢር የለም "እስመ አልቦ ምንትኒ ነገረ ዘይገብር እግዚአብሔር ዘኢከሠተ ወዘኢነበበ ለአግብርቲሁ ነቢያት ""ጌታ

እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባርያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም" አሞጽ 3፡7_8 በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ምስጢሩን ጥበቡን የገለጻላቸው ነቢያት እግዚአብሔር ይወርዳል ይወለዳል ዓለምን ያድናል እያሉ ማዳኑን ሰብከዋል። ይህ የነቢያት ስብከት የነገረ ሃይማኖት ምንጭ ነው "እስመ ተሀነጽክሙ ዲበ መሠረተ ነቢያት" "በነቢያት መሠረት ታንጻችኋል" ኤፌ 2፡20

3ኛ የአምላክ ሰው መሆን ነቢያት በተናገሩት ትንቢት ባስተማሩት ትምህርት መሰረት አምላክ ሰውን ለማዳን በሰጠው ጽኑ ቀጠሮ ሰው ሆኖ መገለጡ የነገረ ሃይማኖት ምንጭ ነው። "ወአመ በጽሐ እድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት" "ጊዜው በደረሰ ጊዜ እነሆ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ"ገላ 4፡4 እንዲል። ሰው ሆኖ ምድርን በኪደተ እግሩ ቀድሶ ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት ፈውሷል "አቡየ ፈነወኒ ወአነ ተፈኖውኩ""አባቴ ላከኝ እኔም ተላኩ ከሰማይ ወረድኩ" ዮሐ ብሎ በማስተማር ነገረ ሃይማኖትን ገለጠልን "እመኑ ብየ ወእመኑ በአቡየ" "በእኔ እመኑ በአባቴም እመኑ " ብሎ አስተማረን። "ነበ እሊአሁ መጽአ ወእሊአሁሰ ኢተወክፍዎ ወለእለሰ ተወክፍዎ ወወሀቦሙ ስልጣነ ውሉደ እግዚአብሔር ይኩኑ ለእለ አምኑ በስሙ""ወደወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም ለተቀበሉት ግን በስሙ አምነው የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው"ዮሐ 1፡12 እንዲህ ብሎ በነገረን መሰረት የነገረ ሃይማኖት ምንጩ የአምላክ ሰው መሆን የሰው አምላክ መሆን የትምህርተ ሃይማኖት ምንጭ ነው።

4ኛ ትምህርተ ሐዋርያት ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ያሉት ተፈጽሞ አምላክ ሰው መሆኑን በዓይን አይተው በዋለበት ውለው ካደረበት አድረው የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት የሰራውን ትሩፋት አይተው ሥቅለቱን ሞቱን ትንሳኤውን እርገቱን ተመልከተው ዳግም ለፍርድ መምጣቱንም ሰምተው ዓለምን በሙሉ ወደ ሃይማኖት ያመጡ ዘንድ ትዕዛዝ ተቀብለው አህዛብን ሁሉ አጥምቀው የሃይማኖት ቤተሰብ አድርገዋል። ነገረ ሃይማኖት በነቢያት ተገልጧል በሐዋርያት ተረጋግጧል "ዘበነቢያት አቅደመ ተአውቆ ወበ ሐዋርያት ተሰብከ" "አስቀድሞ በነቢያት ታወቀ፡/መታወቅን በነቢያት አስቀደመ/ በሐዋርያትም ተሰበከ። " "እስመ ተሐነፅክሙ ዲበ መሰረተ ነቢያት ወሐዋርያት እንዘ ክርስቶስ ማዕዘንተ ህንፃ" ""በነቢያት እና በሐዋርያት መሰረት ላይ ታንጻችኋል የሕንፃው ማዕዘን ማቅኛ ክርስቶስ ነው" ኤፌ 2፡20 እግዚአብሔር የሃይማኖትን ደጅ ከፍቶ በሐዋርያት አሕዛብን ወደ ቤቱ አስገብቷል "አሕዛብም ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ ለዘለዓለም ሕይወትየተዘጋጁ ሁሉ አመኑ የጌታም ቃል በሀገሩ ሁሉ ተስፋፋ" ሐዋ 13፡48 "ጌታም የሚድኑትን እለት እለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር"ሐዋ 2፡47 ይህ የሐዋርያት ትምህርት በሚያደርጉት ተአምራት አሕዛብን ሁሉ ስቧል ወደ እግዚአብሔርም አቅርቧል። ስለዚህም የሐዋርያት ትምህርት ከነገረ ሃይማኖት ምንጮች ትልቁን ስፍራ ይይዛል። ከነዚህ በተረፈ መጻህፍት እና ሊቃውንት የነገረ ሃይማኖት ምንጮች ናቸው """መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ"ማቴ 22፡22

5ኛ ነገረ እግዚአብሔር ፡ ነገረ እግዚአብሔር በሰው አንደበት ተነግሮ በሰው ብዕር ቀለም ተጽፎ የማያልቅ ከውቅያኖስ የጠለቀ ከሰማይ እና ከምድር ሁሉ የራቀ ረቂቃን ከምንላቸው ሁሉ የረቀቀ ነው። ነገረ እግዚአብሔር ማለት ሰው ስለ እግዚአብሔር አዕምሮው የሚሸከመውን ያህል በጥቂቱ ፈጣሪውን ስለማወቅ የሚማረው ትምህርት ማለት እግዚአብሔር የራሱ መገለጫዎች መጠሪያዎች አሉት። በምሥጢረ ሥላሴ

ትምህርት እንደምንማረው እግዚአብሔር የሚለው ስም የሦስቱ አካላት የአንድነት መጠሪያ ስም ነው።“አንሰ ሰብ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ” “እኔ እግዚአብሔር ባልኩ ጊዜ ስለ አብ ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማለቴ ነው”። እግዚአብሔር ማለት ሀያ ሁለቱን ሥነ_ፍጥረት የፈጠረ ማለት ነው “በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ” ዘፍ 1፡1 “እግዚአብሔር ገባሬ ኩሉ ወጣኤ ኩሉ ወፈጻሜ ኩሎ አሀዜ ኩሎ” “ እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረ ሁሉን የጀመረ ሁሉንም የጨረሰ ሁሉንም የያዘ ” ቅዳሴ ማርያም።

## መገለጫዎቹ

**1ኛ ቅዱስ ነው ፡** እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ብለን ስንጠራው ቅድስናው እንደ ፍጡራን በገድል በመከራ የተገኘ ከሌላ የተቀበለው አይደለም ። ቅዱስነት የባህርይው ነው ፡ ቅድስናን ለሌሎች የሚሰጥ ከፍጡራን ቅድስና የተለየ ቅድስና ያለው ነው። የፍጡራን ቅድስና በርኩሰት ይለወጣል እርሱ ሁል ጊዜ የተቀደሰ ነው “ ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ” “እኔ ቅዱስ ነኝ እና እናንተም በሥራችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ“ ዘሌ 11፡44 ”ኩኑ ቅዱሳነ በኩሉ ግዕዝክሙ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ“ ”እኔ ቅዱስ ነኝ እና እናንተም በሥራችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ“ 1ጴጥ1፡15_16 ” “እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና ለእኔ ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ ለይቻችኋለሁና ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ” ዘሌ 20፡26 “ምስጋና እና ውበት በፊቱ ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው” መዝ 96፡6 “እስመ ግሩም ወቅዱስ ውእቱ” “ግሩምና ቅዱስ ነውና” መዝ 99፡3 ኢሳ 6፡2 ።

**2ኛ እንደርሱ ያለ ሌላ ማንም የለም** እግዚአብሔር በአምላክነቱ ብቸኛ የሚመስለው የሌለ ተወዳዳሪ የማይገኝለት አምላክ ነው “አቤቱ በአማልክት (በካህናት በነገሥታት) መካከል እንዳንተ ያለ ማን ነው? ”ዘፀ 15፡11 “በቅድስና የከበረ እንዳንተ ያለ ማን ነው” ዘፀ 15፡16 “ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን ነው? ከአምላካችን በቀር አምላክ ማን ነው? ”1ሳሙ 22፡32 “ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን ነው ? ” መዝ 18፡31 ሌሎችም ብናነብ ይህን የመሰለው ብዙ ነው

**3ኛ ጥበበኛ ነው** ጥበብ ለሌላቸው ሰዎች ጥበብን የሚሰጥ የጥበብ መገኛ እርሱ ነው። “ከእናንተም ማንም ጥበብ የጎደለው ቢኖር በልግስና ከሚሰጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይለምን ይሰጠዋል” ያዕ 1፡5 “በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል አለ” ኢዮ 12፡13_16 “አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው ሁሉንም በጥበብ አደረግህ ምድርም ከፍጥረትህ ተሞላች” መዝ 90፡12 “እግዚአብሔር ምድርን በጥበብ መሰረተ በማስተዋልም ሰማያትን አፀና”ምሳ 3፡29

**4ኛ ሁሉን ቻይ ነው** እግዚአብሔር ሌላ መገለጫው ሁሉን ቻይነቱ ነው። “ሁሉን የሚችል አምላክ ለብዙ ሕዝብ ጉባኤ እንድትሆን ያብዛህ” ዘፍ 28፡3 “እግዚአብሔርም አለው ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ”ዘፍ 35፡11፤ 43፡14 “ ሁሉን የሚችል አምላክ በከነአን ምድር በሎዛ ተገለጠልኝ”ዘፍ 48፡3 “ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንክ አሁን አወቅሁ” ኢዮ 42፡2 ፤ መዝ 91፡1

**5ኛ ዘላለማዊ ነው**

6ኛ ሁሉን ያውቃል

7ኛ የሁሉ ገዢ ነው

ሁሉንም ዘርዝረን ስለማንጨርሳቸው መጻሕፍቱን ማንበብ ይገባናል።

“መንግሥቱ ዘለዓለም ወምኩናኑኒ ለትውልደ ትውልድ” “ሰላም ይብዛላችሁ በመንግሥቴ ግዛት ያሉ ሰዎች በዳንኤል አምላክ ፊት እንዲፈሩ እና እንዲንቀጠቀጡ አዝዣለሁ እርሱ ህያው አምላክ ለዘላለም የሚኖር ነውና መንግስቱም የማይጠፋ ነው ግዛቱም እስከመጨረሻ ድረስ ይኖራል ያድናል ይገድልማል በሰማይና ምድር ድንቅና ተአምራትን ይሰራል ዳንኤልንም ከአንበሳ አፍ አድኖታል” ዳን6፡26 “ወይኴንን እምባህር እስከባህር ወእም አፍላግ እስከ አጽናፈ ዓለም” “ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይገዛል ግዛቱም እስከ ዓለም ዳርቻዎች ነው”መዝ 71፡8 “ስሙ ለዘለዓለም ቡሩክ ይሁን ከፀሐይ አስቀድሞ ስሙ ይኖራል የምድር አህዛብ ሁሉ በርሱ ይባረካሉ ብቻውን ተአምራትን የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ ይባረክ የምሥጋናውም ስም ለዓለም እና ለዘለዓለም ይባረክ ምሥጋናውም ምድርን ሁሉ ይሙላ” መዝ 71፡17 ስለዚህ በስሙ አምኖ ስሙን ጠርቶ በሃይማኖት ለመዳን ስለ እግዚአብሔር ትንሽ ማወቅ ይጠቅማልና ። ሊቃውንትን ጠይቆ መጻሕፍትን አውቆ ድንበሩን ጠብቆ መረዳት ነው እንጂ ስለ እግዚአብሔር ሰው ብዙ ሊያውቅ አይችልም “እግዚአብሔር ታላቅ ነው እኛም አናውቀውም ”ኢዮ 36፡26 እርሱ በፈቀደ መጠን ለሰው ልጆች ይገለጣልና የገለጠልንን የሚገልጥልንንያህል አውቆ አምኖ መኖር ነው “

“አልቦ ዘየአምሮ ለአብ ዘእንበለ ወልድ ወአልቦ ዘየአምሮ ለወልድ ዘእንበለ አብ ወለዘፈቀደ ወልድ ይክስት ሎቱ” “ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም ከወልም በቀር አብን የሚያውቅ የለም ወልድ ለወደደው ይገልጥለታል” ማቴ 11፡27 በዚህ መሰረት ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ የእኛ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን ወሳኙ የ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እንዳንረሳ፡ ሰው እግዚአብሔርን ማወቅ ስለፈለገ ብቻ ሊያውቅ አይችልም እንዲያማ ባይሆን እግዚአብሔርን ማወቅ የማይፈልግ ማን አለ? ፍጡራን ሁሉ በየቦታው የሚኳትኑት እርሱን ፍለጋ አይደል ? መንገዱ ጠፍቷቸው እንጂ። ስለዚህ ፈቃዱን መጠየቅ ይገባል።

# ምዕራፍ ሁለት

# አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

## 2.1 የምስጢር ፍቺ በቤተ ክርስቲያን

ምሥጢር በቤተ ክርስቲያን ራሱን የቻለ ትርጉም አለው። ቤተ ክርስቲያን የምሥጢር ባለቤት እንደመሆንዋ ብዙ ምሥጢራትን ትፈጽማለች። እነዚህን ምሥጢራት ስትፈጽም ዝም ብላ አይደለም ትርጉማቸውን አውቃና ጠንቅቃ ነው። ምሥጢር የሚለው ቃል አመስጠረ አራቀቀ ከሚል የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው።

1ኛ _ስውር ድብቅ

2ኛ_ጥልቅ

3ኛ _ረቂቅ

4ኛ _በልብ ውስጥ የሚኖር

5ኛ _ለማይገባው ሰው የማይነገር

6ኛ_ለሚገባው የሚገለጥ

7ኛ_በእጅ የማይጨበጥ

8ኛ_በዓይን የማይታይ

9ኛ_በተግባር የሚገለጥ

በጠቅላላው ምሥጢር ማለት ለዓይን የራቀ ለልቡና  የረቀቀ አይተው የሚያምኑት ብቻ ሳይሆን አምነው የሚቀበሉት የሚረዱት የሚፈጽሙት በልቡና የሚያኖሩት የሚያስረዱት ተረድተው የሚያስረዱት በእግዚአብሔር አጋዥነት የሚገለጥ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የገለጠው የሚገልጠው ከማያምኑት የሰወረው የሚሰውረው  ምሥጢር ይባላል።

በቤተ ክርስቲያን ምሥጢር የሚባሉት አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ናቸው በሌላ አነጋገር ምሥጢር ማለት ሃይማኖት ነው።

**1ኛ ምሥጢረ  ሥላሴ ምሥጢር ይባላል** ፡ በአካል በስም በግብር  በኩነት ሦስት፤ በባሕርይ በህልውና በአገዛዝ በሥልጣን በመለኮት አንድ ናቸው ብለው ለሰው ይነግሩታል፡ አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ እንደምን ይቻላል ብሎ ልብ ሊመረምረው አንደበት ሊናገረው አይቻልምና ምሥጢር ይባላል።

**2ኛ ምሥጢረ ሥጋዌ ምሥጢር ይባላል፡**  ከሦስቱ አካላት አንዱ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ያለወንድ ዘር ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በህቱም ድንግልና ተጸንሶ በህቱም ድንግልና ተወለደ ብለው ለሰው ነግሩታል፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ ልብ ሊመረምረው አንደበት ሊናገረው አይችልምና ምሥጢር ይባላል።

**3ኛ ምሥጢረ  ጥምቀት ምሥጢር ይባላል፡** ካህኑ ውሃውን በብርት አድርጎ አሀዱ አብ ቅዱስ አሀዱ ወልድ ቅዱስ አሀዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በባረከው ጊዜ ውሃው ተለውጦ  በእለተ ዓርብ ከጌታ ቀኝ ጎን የፈሰሰ ማየ ገቦ ይሆናል ብለው ለሰው ነግሩታል ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ ልብ ሊመረምረው አንደበት ሊናገረው አይችልምና ምሥጢር ይባላል።

**4ኛ ምሥጠረ  ቁርባን ምሥጢር ይባላል፡** ካህኑ ህብስቱን በጻህል ወይኑን በጽዋ አድርጎ አሀዱ አብ ቅዱስ አሀዱ ወልድ ቅዱስ አሀዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በባረከው ጊዜ ህብስቱ  ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ  ደመ መለኮት ይሆናል ብለው ለሰው ነግሩታል ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ ልብ ሊመረምረው አንደበት ሊናገረው አይችልምና ምሥጢር ይባላል።

**5ኛ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ምሥጢር ይባላል፡** ሰው ከሞተ ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ አካል ገዝቶ ኃይል አግኝቶ መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልን ሳይል  ነፍስና ሥጋው ተዋሕደው ይነሳል ብለው ለሰው

ይነግሩታል ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ ልብ ሊመረምረው አንደበት ሊናገረው አይችልምና ምሥጢር ይባላል፡፡

ምሥጢር የተባለበትም ለሚያምኑ የሚገለጥ ለማያምኑ የተሰወረ በመሆኑ ነው "ወለእመኒ ክዱን ትምህርትነ ክዱን ውእቱ ለህርቱማን ወለንፉቃን ወተነብዮሰ ለዘየአምን ወአኮ ለዘኢየአምን""ትንቢት መናግር ለሚያምኑት ነው እንጂ ለማያምኑት አይደለም ወንጌላችን የተከደነ ቢሆንም ለማያምኑት ነው"2ቆሮ 4፡3
ለአዋቂዎች የተሰወረ እውቀት ለሌላቸው የተገለጠ ነው "እስመ ሀባእኮ ለዝንቱ እም ጠቢባን ወእማእምራን ወከሰትኮ ለህጻናት" "ከአዋቂዎች ሰውረህ ለህጻናት ገልጠኸዋልና"ማቴ 11፡28
"ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስ ባዕለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር የተሰወረው የሥርዓት ምሥጢር ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ለማንስ ለእኔ ተገለጠ " 1ቆሮ 3፡8 በዚህ መሰረት ለቅዱሳን አበው የተገለጠ ምሥጢር ሃይማኖት ነው፡፡ ይህን ከልቡና ከመጻሕፍት ከመምህራን መርምሮ መቀበል ነው ፡፡

## 2.2 ምሥጢረ ሥላሴ ፡

ምሥጢረ ሥላሴ የሚባለው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት አንዱ ነው፡ ይህም የቤተ ክርስቲያን መሰሶዎች ተብለው ከሚጠሩት የመጀመርያው ነው "እፈቅድ እንግር አምስተ ቃላተ አዕማዲሃ ለቤተ ክርስቲያን" "ለቤተ ክርስቲያን መሰሶዎች የሆኑ አምስት ቃላትን ልናገር እወዳለሁ" 1ቆሮ 14፡19
ዓለም ሳይፈጠር ዘመን ሳይቆጠር በአንድነት በሦስትነት ጸንቶ የሚኖር በአንድነቱ ምንታዌ (በአንድነቱ መንታነት) በሦስትነቱ ርባኤ (በሦስትነቱ አራትነት) ሳይኖርበት የኖረ ያለ የሚኖር እግዚአብሔርን የምናውቅበት ትምህርት የመጀመሪያው ምሥጢረ ሥላሴ ይባላል፡፡ ይህን ምሥጢር ዓለም እና አለቆቹ ሊያውቁት አልቻሉም ረቂቅ ነውና፡ ጥበበ እግዚአብሔር ነውና "ጥበበ ንነግሮሙ ለጠቢባን ወአኮ ጥበበዝ ዓለም ወኢጥበበ መላዕክተ ዝንቱ ዓለም ዘሀለዎሙ ይሰአሩ""ጥበብን ለጥበበኞች እንነግራቸዋለን ጥበቡም የዚህ ዓለም ጥበብ አይደለም ይሻሩ ዘንድ ያላቸው የዚህ ዓለም ገገርዎች ጥበብ አይደለም" 1ቆሮ 2፡6 ፡

በቤተ ክርስቲያን አዕማደ ምሥጢር የሚባለው ትምህርት የሁለት ቃላት ውጤት ነው አዕማድ እና ምሥጢር ከሚሉ፡፡ አዕማድ ማለት መሰሶዎች ማለት ነው፡፡ ምሥጢር ማለት ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው ነው፡፡ መሰሶ ቤቱን ተሸክሞ አጽንቶ እንዲኖር እነዚህም የሰውን ቤተ ልቡና በሃይማኖት አጽንተው ተሸክመው የክህደት ነፋስ እንዳይጥለው ደግፈው የሚኖሩ ስለሆነ አዕማድ ይባላሉ፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው አምድ ምሥጢረ ሥላሴ ነው፡፡

ምሥጢረ ሥላሴ ማለት የእግዚአብሔርን አንድነት ሦስትነት የምንማርበት የትምህርት ክፍል ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው፡፡ ሥላሴ ማለትም ልዩ ሦስትነት ማለት ነው፡፡ ልዩ ሦስትነት ማለትም አንድ ሲሆን ሦስትነት ያለው ሦስት ሲሆን አንድነት ያለው ማለት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ምሥጢረ ሥላሴ ተብሎ ይጠራል፡፡ በቅደም ተከተል አቅማችን በፈቀደ መጠን ይህንን ትምህርት መማር ለክርስቲያኖች የግድ ያስፈልጋል፡፡

ምሥጢረ ሥላሴ የሦስትነት ምሥጢር የማይመረመር መለኮት ቅድመ ዓለም የነበረ ወደፊትም የሚኖር አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የተባሉ አካላትን በማዋሐድ እግዚአብሔር በአካል በስም በገጽ በግብር በኩነት/ሁኔታ ሦስት በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድ መሆኑን የምናምንበት የምንማርበት የምናስተምርበት ክፍል ነው።

እግዚአብሔር ወይም ሥላሴ አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት አበው ሊቃውንት ያስረዳሉ አነጋገራቸው እግዚአብሔር በአካል ሦስት ሲሆን በባሕርይ አንድ ነውና ባለቤቱን አንድ አድርገው ይናገራሉ ይኸውም እንደሚከተለው ነው።

"ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበ አምሳሊነ"እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌያችን እንፍጠር አለ"ዘፍ 1፡26
"ወይቤ እግዚአብሔር አዳም ኮነ ከመ አሀዱ እምኔነ""አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አለ እግዚአብሔር " ዘፍ 3፡26 እያለ ባለቤቱን አንድ አንቀጹን አንድ ሃሳቡን ዝርዝሩን የብዙ እያደረገ እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ሦ ስት ሲሆን አንድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል።

"ወይቤ እግዚአብሔር ንዑ ንረድ ወንከአው ነገሮሙ ለከለዳውያን" "ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን እንደባልቀው አለ እግዚአብሔር " ብሎ ከላይ ያየነውን ምስክርነት የፀናዋል ዘፍ 11፡6
ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በየሥርዓቱ በየአይነቱ ያስረዳልና ማንበብ ነው።

## የአካል ሦስትነት

እግዚአብሔር በአካል ሦስት ነው በአካሉ በገጹ መጠቅለል መቀላቀል መፋለስ የሌለበት ልዩ ሦስት ነው በባሕርይ አንድ ሲሆን በአካል በገጽ ሦስት መሆኑን ራሱን በራሱ መሰወር ራሱን በራሱ መግለጥ የሚችል አምላክ ገልጧል መጀመሪያ ለአበው በአብርሃም በዘመነ ሥጋዌ ለዓለም በሙሉ ራሱን ገልጦ አስረድቷል።
ምንም እንኳን የሰው ልጅ ባጠፋው ጥፋት በበደለው በደል የእግዚአብሔርን ፊት ሊያይ ባይችልም ሃይማኖቱ ለቀና ምግባሩ ለጸና ለአብርሃም ያየው ዘንድ ራሱን ወድዶ እና ፈቅዶ ገለጠለት አንድም ሦስትም መሆኑ ይታወቅ ዘንድ።
"በቀትር ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት ዓይኑንም አነሳና እነሆ ሦስት ሰዎችን አየ"ዘፍ18፡1
ከላይ ባለቤቱን እግዚአብሔር እያለ አሳቡን የብዙ እያደረገ መጥቶ መጽሐፍ ጭብጡን አይለቅምና ?ለሽፋጭ አይመችምና አሁንም ባለቤቱ እግዚአብሔር ተገለጠለት ብሎ አንድ ሦስት ሰዎችን አየ በማለት እግዚአብሔር ሦስት መሆኑን አረጋግጧል።
"ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነስቶ ሮጠ ወደምድርም ሰገደ እንዲህም አለ አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ ባርያህን አትለፈኝ " "አቤቱ" እና "አትለፈኝ" የሚለው አንድነቱን የሚገልጡ ናቸው

"ሦስት ሰዎችን አየ" የሚለው ሦስትነቱን ያስረዳል። ሦስት ሰው "አትለፉኝ" እንጂ "አትለፈኝ" አይባልም፡ "በፊታችሁ" እንጂ "በፊትህ" አይባልም፡ በአካል በገጽ ሦስት፡ በአገዛዝ በሥልጣን በአምላክነት አንድ ነውና "አትለፈኝ" አለው። ይህንን ምዕራፍ ሙሉውን ብናነበበው የሚገልጠው ይህንኑ ነው።

ከአብርሃም ቤት ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንነለሁ ብሎ ለአዳም የሰጠውን ተስፋ ደገመው "እንደዛሬ የዛሬ ዓመት ወደ ቤትህ እመጣለሁ" ብሎ ለጊዜው ይስሐቅ በፍጻሜው ግን ቤዛ ይስሐቅ ክርስቶስ እንዲወለድ አስረዳው ተስፋ አበው የሚባለው ይህ ነው። ይህ ተስፋ ዘመኑ ደርሶ ሲፈጸም ለአብርሃም የተገለጠ አንድነት እና ሦስትነት በሰፊው ተገለጠ፡ በአብርሃም ራሱን የገለጠ አምላክ ለነቢያት በብዙ ሕብረ መልክ ተገልጦ አንድነቱን ሦስትነቱን ገልጧል።

"ወእምዝ በዓመተ ሞተ አዝያን ንጉሥ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ነዋህ ወብሩህ " "ንጉሡ አዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁት" ኢሳ 6፡1 ብሎ አንድነቱን ነግሮን "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ የተነሳ ሞልታለች" ብሎ አንድነቱን ገልጦ ሦስትነቱን አስረግጦ ምልአቱን ጥልቀቱን ስፋቱን እርሱ ስለ በመላእክትና ፍጥረታት ላይ ጌታ ገዥ በሁሉ የሰለጠነ መሆኑን ጨምሮ አስረድቷል። በዚህ መሠረት የአካል ሦስትነቱ የተረጋገጠ ነው "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ" የሚለው ደጊመ ቃል የዕብራውያን ልምድ የሚመስላቸው አይጠፉም። ይህ ደጊመ ቃል አይደለም፡ ምክንያቱም ደጊመ ቃል ሁለት ጊዜ ነው፤

ለምሳሌ :

"ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም" ማቴ 23፡37

"እውነት እውነት" ዮሐ 10፡1

"አብርሃም አብርሃም"

"ማርታ ማርታ "ሉቃ 10፡23

"ኤሎሄ ኤሎሄ" ማቴ 27

"አምላኬ አምለኬ"

"አልአዛር አልአዛር" ዮሐ 11፡43

"ሙሴ ሙሴ" ዘፀ 3፡4

**የሚሉትን የመሰሉ ደጊመ ቃል ይባላሉ።**

"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ" የሚሉት ዝቅ ብለው ሁለት፡ ከሦስት አልፈው አራት የማይሆኑ፡ አንድነት የቃል ለውጥ ባለማሳየት ሦስትነትን ሦስት ጊዜ በመባል የሚያስረዱ ናቸው። ምሥጢር ያላቸው እንጂ ለጽሁፍ ለቃላት ውበት የተቀመጡ አይደሉም። እነዚህን መሰል ቃላት በብዛት አሉ፡ ወይ በአንድ አሊያ በሦስት ብቻ ነው። ይህ በቅጽል መልክ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ተሰጥተው እናገኛለን።

"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረው እና ያለው" ራዕ 4፡2

"ኦ አባ ቅዱስ እቀቦሙ ከመይኩኑ እሙንቱሂ ቅዱሳነ በጽድቅ" "ቅዱስ አባት ሆይ ጠብቃቸው" ዮሐ 17፡11

"ወመንፈሰከ ቅዱሰ ኢታውጽእ እም ላዕሌየ" "ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ" መዝ 50

"በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ስም ምልክት እና ድንቅ ሲደረግ ባርያዎችህ በፍጹም ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው"

ለሦስቱም አካላት ተጠቅሷል ፡ እግዚአብሔር በአካል ሦስት በቅድስና በአምላክነት አንድ ነው፡ በዚህ እግዚአብሔር በአካል ሦስት ስለመሆኑ ምስክሩ ብዙ ነው፡ ጥቂቶችን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡
ግን አካል አለው አካሉም ምሉዕ ስፉህ ረቂቅ ኢሀማሚ የማይደክም የማይዝል የማያረጅ ዘላለማዊ ነው፡፡

**የአካል ወይም የገፅ ሦስትነት የምንለው**

ለአብ ፍጹም አካል አለው
ለወልድ ፍጹም አካል አለው
ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል አለው በዚህ አካል መጠቅለል መቀላቀል ሳይኖርበት ጸንተው የነበሩ ያሉ ናቸው፡፡
ይህ የአካል ሦስትነት በአብርሃም ቤት ለአብርሃም በዘመኑ ለኢሳይያስ አምላክ ሰው በሆነበት ዘመን ለሁሉ ተገልጧል፡፡

**ለምሳሌ**

"ወተጠሚቆ እግዚእ ኢየሱስ ሶቤሃ ወጽአ እማይ ወናሁ ተርህወ ሎቱ ሰማይ ወርዕየ መንፈሰ እግዚአብሔር እንዘ ይወርድ እም ሰማይ በአምሳለ ርግብ ወይነብር በዲበ ርዕሱ ለእግዚእ ኢየሱስ ወመጽአ ቃል እም ሰማይ ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር" "ኢየሱስም ከተጠመቀ በኂላ ወዲያው ከውሃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ሲወርድ በራሱም ላይ ሲቀመጥ አየ እነሆም ድምጽ ከሰማይ መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት" ማቴ 3፡16 ሲል መሰከረ በዚህ አንድነት ሦስትነት ተገልጧል፡፡ አንዱ አካል ወልድ ሲጠመቅ ታይቷል መንፈስ ቅዱስ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አብ ሲናገር ተሰምቷል ይህን እንዴት ሊሆን ይቻላል ሳንል አምነን መቀበል ነው፡፡

አካላዊ መሆኑን መጻሕፍት ያስረዳሉ
"የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸው ጆሮዎቹም ወደ ልመናዎቻቸው" መዝ 37
"ሰማይኒ መንበርየ ወምድርኒ መከየደ እገርየ እዴየ ሳረረታ ለምድር የማንየ አጽንአቶ ለሰማይ አኮኑ እደውየ ገብራ ዘኩሎ"
"እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም"ኢሳ 59፡1
"ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት እነዚህን ሁሉ እጄ ሰርታለች እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር "ኢሳ 66፡1_3 እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ባይ አካል ያለው ዓይን ገፅ እጅ እግር ሙሉ አካል ያለው መሆኑን ገላጭ ናቸው፡፡
"ሀሰስኩ ገጸከ ገጸዚአከ አሀሥሥ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ" "ፊትህን ፈለግኩ አቤቱ ፊትህን እሻለሁ ፊትህን ከእኔ አትመልስ"መዝ 26፡8
ይህም ሦስት ጊዜ ፊትህ ፊትህን ፊትህ የሚለው የገጽ ሦስትነቱን ሲያሳይ ፊትህን ከእኔ አትመልስ የሚለው አንድነቱን ያሳያል፡፡

## የስም ሦስትነት

የአካል ሦስትነት እንዳለው ሁሉ እግዚአብሔር የስም ሦስትነት አለው። ይህም ስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብለን የምንጠራው፡ ሃይማኖትን የምንገልጽበት፡ አምነን የምንጠመቅበት፡ ሰይጣንን የምናሸንፍበት ስም ነው። ”ሁሩ ወመሀሩ ኩሎ አሕዛበ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ“ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ እያስተማራችሁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀመዛሙርት አድርጉ” ማቴ 28፡19

ቀድሞ ለአብርሃም በመምሬ የአድባር ዛፍ በቀትር ጊዜ የተገለጠለት ኋላም ለዮሐንስ በዮርዳኖስ የተገለጠለት አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። በዚህ ስም ከመጠራቱ በፊት እግዚአብሔር በባህርይ ስሙ ሦ ስቱም በሚጠሩበት ስም እግዚአብሔር አምላክ እየተባለ ይጠራ ነበር። አልፎ አልፎ በብሉይ ኪዳን ስማቸው ለየብቻ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እየተባለ ቢጠራም በብዛት እግዚአብሔር በሚለው ስሙ ይጠራ ነበር። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለውን አንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ገለጠው።በዚህ ስም እንጠራው ዘንድ።

”ስማእ እስራኤል አሀዱ ውዕቱ አምላክከ“ ”እስራኤል ሆይ ስማ ፈጣሪህ እግዚአብሔር አንድ ነው“ ዘዳ 6፡4

አካላት በሦስትነት ቢገለጡም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብሎ መጥራት አልተለመደም ምክንያቱም በብዛት አልተገለጠም ነበርና ፡ በጥቂቱ ግን ተነግሯል፡

”አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ የፈጠረህ እርሱ አብ አይደለምን? “ዘዳ 32፡6

”ወራብኡሰ ይመስል ወልደ እግዚአብሔር አራተኛውስ የእግዚአብሔር ልጅ ይመስላል“ዳን3 ፡25

ስለ እግዚአብሔር አብና ወልድ

”መንፈስ ቅዱስ በርብቃ አፍ ላይ ወረደ“ ኩፋሌ 19

ይህን በብሉይ ኪዳን በተለያየ መልኩ የተገለጠው የስም ሦስትነት ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ላይ ሰብስቦ ”በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው“ ብሎ የእምነታችን መገለጫ በአንድነት ስሙ ላይ ጨመረልን ገለጠልን ማለት ነው።

በኦሪት ላይ ወንጌልን በመንፈሰ ረድኤት ላይ መንፈስ ልደትን እንደሰጠን እግዚአብሔር ብለን የምንጠራው በተጨማሪ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብለን እንድንጠራ ስሙን አስተማረን። እግዚአብሔር የሚለው የሦስቱም ስም ነው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይጠሩበታል።

”አንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ“

”እኔ እግዚአብሔር ባልኩኝ ጊዜ ስለ አብ ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማለቴ ነው“ ቅዱስ ባስልዮስ ዘአንጾኪያ ሃይማኖተ አበው ምዕ 96፡4

"ወሶበሂ ንብል አሀዱ እግዚአብሔር ወአሀዱ መለኮት ንብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" "አንድ እግዚአብሐር አንድ መለኮት ስንል ስለ አብ ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ መናገራችን ነው“ ሃአ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ምዕ 107 ክፍል 1

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለው ስም ግን ተፋልሶ የለበትም አብ የሚለውስም አብ ብቻ ይጠራብታል ወልድ የሚለው ስም ወልድ ብቻ ይጠራብታል መንፈስ ቅዱስ የሚለው ስም መንፈስ ቅዱስ ብቻ ይጠራብታል።

" ኢይፈልስ ስመ አብ እምከዊነ ስመ አብ ሀበከዊነ ስመ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወስመ ወልድኒ ኢይፈልስ እምከዊነ ስመ ወልድ ሀበከዊነ ስመ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ወስመ መንፈስ ቅዱስኒ ኢይፈልስ እምከዊነ ስመ መንፈስ ቅዱስ ሀበ ከዊነ ስመ አብ ወወልድ ""የአብ ስም አብ ከመባል ወልድ መንፈስ ቅዱስ ወደመባል የወልድም ስም ወልድ ከመባል አብ መንፈስ ቅዱስ ወደ መባል የመንፈስ ቅዱስ ስም መንፈስ ቅዱስ ከመባል አብ ወልድ ወደ መባል አይፋለስም አይለወጥም "ሃአ

" አብኒ አብ ውእቱ ወልድኒ ወልድ ውእቱ መንፈስ ቅዱስኒ መንፈስ ቅዱስ ውእቱ አብኒ ኢኮነ ወልደ ወኢ መንፈስ ቅዱሰ ወልድኒ ኢኮነ አበ ወኢመንፈስ ቅዱሰ ወመንፈስ ቅዱስኒ ኢኮነ አብ ወኢ ወልደ"" አብ አብ ነው ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይባልም ወልድም ወልድ ነው አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ነው አብ ወልድ አይባልም አብም ወልድን መንፈስ ቅዱስን አይደለም አብ ነው ወልድም ወልድ ነው እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይደለም መንፈስ ቅዱስ አብ ወልድ አይደለም መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ "ሃይ አበ

## የግብር ሦስትነት

እግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ የስም ሦስትነት እንዳለው ሁሉ የግብር ሦስትነት አለው። ግብር በሁለት ይከፈላል የአካል ግብር እና ሥልጣናዊ ግብር ተብሎ ።

አሁን የምንመለከተው የአካል ግብርን ነው፡ የአካል ግብር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያልነው የስም ትርጉም ነው።

አብ አባት ነው ግብሩ መውለድ ፡ ማስረጽ /ማስገኘት/ ወላዲ የወለደ ያስገኘ አስራጺ ነው።

የወልድ ግብሩ መወለድ ነው፡ ተወላዲ /የተወለደ/ ማለት ነው

መንፈስ ቅዱስ ግብሩ መስረጽ /መገኘት/ ነው ሰራጺ ይባላል /የወጣ የተገኘ/ ቅድም በስም እንዳየነው ሁሉ የግብር ተፋልሶም የለም በሥላሴ።

- **አብ ወላዲ**
- **ወልድ ተወላዲ**
- ***መንፈስ ቅዱስ ሰራጺ*** እየተባሉ ይኖራሉ አብ ወላዲ እንጂ ተወላዲ ሰራጺ አይባልም ወልድም ተወላዲ እንጂ ወልድ አሰራጺ አይባልም መንፈስ ቅዱስም ሰራጺ ይባላል እንጂ ወላዲ ተወላዲ አይባልም በየራሳቸው ስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ በየራሳቸው የአካል ግብር ወላዲ ተወላዲ ሠራጺ ተብለው ፀንተው ይኖራሉ በስም በግብር በአካል ሦስት ማለት ይህ ነው።

ይህ የአካል ግብራቸው በመጻሕፍት ተገልጧል ማንበብ ነው።

የአብ አባትነት ወይም ወላጅነት የወልድ ልጅነት /ተወላዲነት/

- "ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ ውእቱ አቢይ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ስሙን ኢየሱስ ትለዋለች እርሱ ታላቅ ነው የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሉቃ 1፡3
- "እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስከመስጠት ደርሶ ዓለሙን እንዲህ ወዷልና" ዮሐ 3፡16

- “አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክቡር የሆነውን ክብሩን አየን” ዮሐ 1፡14
- “አቡየኒ እስከ ይዕዜ ይገብር ወአነሂ እገብር አባቴ እስከ ዛሬ ይሰራል እኔም እሰራለሁ” ዮሐ 5፡17_18
- “ወመልአ መንፈስ ቅዱስ ላእለ ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ በኤልሳቤጥ ሞላ” ሉቃ 2፡
- “ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል” ዮሐ 14፡16
- “ከአብ የወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል” ዮሐ 15፡26

በዚህ መልክ በራሳቸው የአካል ግብር ጸንተው ይኖራሉ።

*ሥልጣናዊ ግብር የሚለውን በስልጣን ያላቸውን አንድነት ስናይ እናየዋለን።*

## የኩነት / የኊኔታ/ ሦስትነት

ኩነታት በተፈልጠ  በተከፍሎ ያለመጠቅለል ያለመቀላቀል በራሳቸው ጸንተው የሚኖሩ አካላትን በሕልውና የሚያገናዝቡ ናቸው።

እነርሱም ልብነት ቃልነት እስትንፋስነት ተብለው ይጠራሉ ወይም ልብ መሆን ቃል መሆን እስትንፋስ መሆን ማለት ነው።

ልብነት በአብ መሰረትነት ለራሱ ልባዊ ሆኖ ለወልድ እና  ለመንፈስ ቅዱስ ልብ እውቀት መሆን ነው። ቃልነት በወልድ መሠረትነት ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ መሆን ነው፡እስትንፋስነት በመንፈስ ቅዱስ መሰረትነት እራሱ ሕያው ሆኖ ለአብ እና ለወልድ ሕይወት መሆን ነው፡ ይህ ኩነታት ይባላል።

በዚህ መሰረት ምሥጢረ  ሥላሴ የሚያስተምሩ ሊቃውንት አብ በልብ ወልድ በቃል መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ መስለው ያስተምራሉ።

በአብ ልብነት ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያስቡበታል ፡ በወልድ ቃልነት አብ መንፈስ ቅዱስ ይናገሩበታል፡ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት አብ ወልድ ሕልዋን ናቸው ይኖሩበታል።

“አብኒ ልቡናሆሙ ለወልድ ወለመንፈስ ቅዱስ ወልድኒ ቃሎሙ ለአብ ወለመንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስኒ እስትንፋሶሙ ለአብ ወወልድ” ሃይ አበ

“አብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው እስትንፋሳቸው ነው ወልድ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው /ሕይወታቸው/ ነው። በአብ ልብነት ያስባሉ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይኖራሉ ማለት ነው።”

ይህን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በሚከተሉት ምሣሌዎች መስለው ያስተምራሉ

1_በነፍስ

2_በፀሐይ

3_በእሳት

**1_በነፍስ**

ነፍስ አካሏ አንድ ሲሆን ሦስት ከዊን አላት  ልብ ቃል እስትንፋስ

ልብ ቃል እስትንፋስ ያላት ነፍስ የሦስትነቷ ከዊን አንድነቷን እንደማይከፍል የአንድነቷ ከዊን ሦስትነቷን እንደማይጠቀልለው ሥላሴም በአካል በስም በግብር በከዊን ሦስትነታቸው አንድነታቸውን ሳይከፋፍለው አንድነታቸውም ሦስትነታቸውን ሳይጠቀልለው ልዩ ሦስት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እንላቸዋለን። ነፍሳችን ልብ ቃል እስትንፋስ ስላላት ሦስት ነፍስ እንደማትባል ሥላሴም በአካል በሥም በግብር ሦስት ብንልም ሦስት አምላክ አይባልም አንድ አምላክ እንጂ" ሃይ አበ

"ወኢይትበሀሉ ሠለስተ አማልክተ አላ አሀዱ አምላክ" "ሦስት አምላክ አይባሉም አንድ አምላክ እንጂ"

**2_በፀሐይ**

ፀሐይ ሦስት ከዊን/ሁኔታዎች/ አሏት። ክበብ ብርሃን ሙቀት።

ክበቡ በክበብነቱ ሙቀትን ብርሃንን ያስገኛል፡ ብርሃንም በክበቡ መሰረትነት ከክበብ ተገኝቶ ለዓለም ያበራል የጨለማን ሥልጣን ይሽራል ሙቀትንም በክበብ መሠረትነት ተገኝቶ እርጥቡን ያደርቃል ቅዝቃዜን ያስለቅቃል።

በክበቡ አብ በብርሀኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ይህ ሦስት ሁኔታዎች ያሉት ፀሐይ ሦስት ፀሐይ እንዳይባል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሦስት ሲሆኑ አንድ አምላክ ይባላሉ።

**3_በእሳት**

እሳት አካሉ አንድ ነው ሦስት ሁኔታዎች አሉት፡ እነርሱም ነበልባል ብርሀን ዋዕይ /ሙቀት/ ናቸው። በነበልባሉ አብ በብርሀኑ ወልድ በዋዕዩ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ይህ አንድ እሳት ይባላል እንጂ ሦስት እሳት እንዳይባል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል በስም በግብር በኩነት ሦስት ቢሆንም አንድ አምላክ ይባላሉ እንጂ ሦስት አምላክ አይባሉም።

ከላይ የተመለከትናቸው ሦስትነቶች በህልውና ተገናዝቦ አንዱ በአንዱ ሕልው ሆኖ አንዲት ስግደት ተሰግዶላቸው አንድ አምልኮት ተሰጥቷቸው ይኖራሉ አንድ አምላክ ተብለው ይመለካሉ።

- አብ ፈጣሪ ነው ወልድም ፈጣሪ ነው መንፈስ ቅዱስም
- "አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ" "የፈጠረህ አብ አይደለምን? " ዘዳ 32፡
- "ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ" ዕብ 1፡2
- "ሁሉ በእርሱ ሆነ" ዮሐ 1፡3
- "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ" ኢዮ 33፡4

ሦስቱን አንድ እግዚአብሔር አንድ ፈጣሪ ብለን እናምናለን።

በአካል በስም በግብር በኩነት ሦስት በባህርይ በህልውና በሥልጣን አንድ አምላክ ብለን እናምናለን።

- "አነ ወአብ አሀዱ ንህነ" "እኔና አብ አንድ ነን" ዮሐ 10፡30
- "ዘርእየ ኪየ ርእዮ ለአቡየ" "እኔን ያየ አብን አየ" ዮሐ 14፡8
- "ወበዝሁ ሕዝብ በትምህርተ መንፈስ ቅዱስ" ሐዋ
- "ይህ የምትሰሙት ቃል የእኔ አይደለም" ዮሐ

- “ትምህርቴ ከእኔ አይደለም” ዮሐ
- “የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ሁሉን ከእኔ ወስዶ ያስተምራችኋል”

የሚሉት የሕልውናን አንድነት የሚያሳዩ እኩል እሩያን እንደ ሆኑ የምንማርባቸው ናቸው።
ይህ ምሥጢረ ሥላሴ ይባላል።

አብ አባት ነው ከወልድ አይቀድምም አይበልጥም ከመንፈስ ቅዱስም አይበልጥም አይቀድምም ወልድ ልጅ ነው ከአብ አያንስም ከመንፈስ ቅዱስ አይበልጥም መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከወልድ አያንስም።
ምሥጢር ያሰኘውም ይህ ነው። ሦስት ናቸው አንድ አምላክ። አባቱ ነው አይበልጠውም መቀደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ የለም።
“አሀቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወእሩያን እሙንቱ በቅድምና ለሥላሴሰ አልቦ ቅጽበት ከመ ቅጽበተ ዓይን”
“ለሥላሴ ቅድምናቸው አንዲት ናት ቅድመ ዓለም በመኖር የአይን ጥቅሻ ያህል አይቀዳደሙም” ሃይ አበ ኤራቅሊስ።

ይህን ተቀብሎ መኖር ምሥጢር ነው። አባት ከሆነ እንዴት አይቀድምም ልጅስ ከሆነ እንዴት አያንስም አስገኝ ነውና ይቀድማል ከርሱ የተገኘ ነውና ያንሳል አይባልም አይመረመርም ከህሊና በላይ ነው። እንዴት ወለደው እንዴት አስገኘው ግሩም ምሥጢር በዕጹብ የሚወሰን መልሱ እጹብ ነው።
“ልደተ ወልድ እም አብ ወጸአተ መንፈስ ቅዱስ ኢይትነገር አላ ይትነከር” ሃይ አበ ቴዎዶስዮስ
“የወልድ ከአብ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መገኘት ይደነቃል እንጂ አይመረመርም” ሃይ አበ። ከዚህ የተነሳ ምሥጢር ይባላል። ይግለጥልን።

## 2.3 ምሥጢረ ሥጋዌ

ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት የሰው አምላክ የመሆን ምሥጢር ነው።”ተሰገወ“ ሰው ሆነ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተወሰደ ነው።
ይህም የአምላክ ሰው መሆን የሰውን አምላክ መሆን ምሥጢር የምንማርበት ነው። ይህም ከሦስቱ አካላት /አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ/ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ በጥንት ግብሩ ለመጽናት እና ለመጠራት ሰውን ከዲያቢሎስ ባርነት ከነጢያት እስራት ነጻ ያወጣው ዘንድ ሰው መሆኑን የምንማርበት ምሥጢር ነው ምሥጢረ ሥጋዌ።

ለነገረ ሥጋዌ ምክንያቱ የሰው ልጅ ውድቀት ነው፡ እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ በገነት አኖረው። በፍጥረት ሁሉ አሰለጠነው ከአንዲት ዕፀ በለስ በስተቀር ሁሉን ግዛ ንዳ ብላ ጠጣ ብሎ አስረከበው።
ሰውም ምክረ ከይሲን ሰምቶ እፀበለስን በልቶ ከፈጣሪው ተጣልቶ ከመላዕክት ህብረት ከሥላሴ ልጅነት ወጥቶ የዲያቢሎስ ባርያ ሆነ ከግነት በመውጣቱ ከእግዚአብሔር በመለየቱ አዳም ንስሐ ገብቶ አለቀሰ ለፈጣሪው መስዋዕት አቀረበ ፈጣሪውም አዳምን ”በአምስት ቀን ተኩል ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሀለሁ“ ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት። ይህን ተስፋ ሰጠው ይህንም በልዩ ልዩ መልኩ በነቢያት ትንቢት ተነገረ ሱባኤ

ተቆጠረ።

" አዳም ኮነ ከመ አሀዱ እምኔነ "" አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ "ዘፍ3፡22

የአምላክ ሰው የመሆን የትንቢት መጀመሪያ ነው።

" ነቢየ ያነስእ ለክሙ እግዚአብሔር ዘከማየ ወሎቱ ስምዕዎ "" ከመካከላችሁ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል እርሱን ስሙት "

" እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች "ኢሳ 7፡14

" ሕጻን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለን "" ህጻን ተወለደልን ብላቴናም ሆኖ ተሰጠልን "ኢሳ 9፡9

ብዙ ነቢያት ይህን ተስፋ ትንቢት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመንተናገሩ ተስፋውን ለሰው ልጅ አሰሙ።

ጊዜ ሲደርስ አምባ ይፈርስ እንዲሉ ዘመኑ ሲደርስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ተልኮ የምስራቹን ነገራት።

" ወበሳድስ ወርህ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምሀበ እግዚአብሔር "" እነሆ በስድስተኛው ወር ገብርኤል መልአክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ ከአንዲት ሀገር ናዝሬት ገሊላ ከምትባል ከድንግል ዘንድ የዚያችም ድንግል ስሟ ማርያም ነው "ሉቃ 1፡26 ይህ የተስፋ ትንቢት የተፈጸመው በእመቤታችን ነው ሉቃ 1፡26

ወደ እመቤታችን ቀርቦ ደስታ ይገባሻል በማለት ብስራቱን ሲጀምር እመቤታችን እንዲህ ያለ ሰላምታ አለን ? አባቴ አዳምን እናቴ ሔዋንን ያሳተ ጠላት ሊያስተኝ ነው ብላ ቃሉን እንዲሁ ዝም ብላ አልተቀበለችም እርሱም ጉዳዩን ለማስረዳት ብዙ ምስጋና አቅርቦላት ብዙ ሰላምታ ሰጥቷት

" ትፀንሲ ተወልዲ "" ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ "አላት፡ እመቤታችንም " እምአይቴ ረከብከ ዘከመዝ ብስራተ እንበለ ዘር ምድር እትወተ ወዘእንበለ ምት እምድንግል ፅንሰት"" ምድር ያለዘርታበቅል ሴትም ያለወንድ ትፀንስ ዘንድ ይህ እንዴት ይሆናል? "አለችው፡

"መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል" "መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኃይል ይጋርድሻል ይህ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው"

እነሆ ዘመድሽ የምትሆን ኤልሳቤጥ እንኳን ፀንሳለች ልጅም አገኘች እነሆ ይህ ስድስት ወር ሆነ ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና።

ማርያም አለች እንደ ቃልህ ይደረግልኝ እኔ ለእግዚአብሔር ባርያው ነኝ" ሉቃ 1፡26_49

ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ ዋሕድ ቃል እግዚአብሔር በማህፀኗ አደረ። ተፀነሰ።

" አኮ በመልአክ ወአኮ በተንባል አላ ለሊሁ ይመፅእ ወያድኅነነ "" በመልአክ አይደለም በአማላጅ አይደለም ራሱ መጥቶ ያድነናል "ኢሳ 63።1

ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ እርሱ በሚያውቀው ሰው በማያውቀው ከህሊና ፍጡራን በላይ በሆነ ጥበቡ ከድንግል ተጸነሰ።

የዲያቢሎስን ሥራ ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ በሚበልጥ ጥበቡ ሥጋን ለብሶ ሰው ሆኖ ያፈርሰው ዘንድ

" ወበእንተዝ አስተርአየ ወልደ እግዚአብሔር ከመይስአር ግብሮ ለጋኔን "እንዲል ዮሐ 3፡7

" የዲያቢሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ "

የዲያቢሎስን ሥራ ያፈረሰው በእለተ ጽንስ ጀምሮ ነው። በፅንስ ቁራኝነት አጠፋ ሰው የሚጸነሰው በዘር በደም ነው ዲያቢሎስ በዚህ ተቆራኝቶት ይወለድ ነበር።
ጌታችን መንገድ ለወጠበት፡ በድንቅ ጥበቡ መንገድ ለወጠበት ያለዘር ያለ ሩካቤ በድንግልና ተጸነሰ የሚቆራኝበት ምክንያት አሳጣው። በሩን ዘጋበት። በዚህ ቁራኝነቱን ሻረ።
" መርገመ ወሰአረ እምዘመድነ "" በዘመዶቻችን አድሮ የነበረ መርገም ሻረ "እንዲል ሊቁ።
" ቃል ሥጋ ኮነ ወሀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመስብሐተ አሀዱ ዋህድ ለአቡሁ ዘምሉዕ ፀጋ ወክብረ ወሞገሰ "" ቃል ሥጋ ሆነ ፀጋ እና ክብርን ተመልቶ በእኛ አደረ ለአባቱ አንድ እንደሆነ ልጅ ክብሩን አየን "ዮሐ 1፡14

ሥጋ ሆነ ማለት ሰው ሆነ ማለት ነው።
ከሁለት አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ሆነ የቃል ገንዘብ አምላክነቱ ገገርነቱ ምልአቱ ሥፍሐቱ ለሥጋ ሆነ የሥጋ ገንዘብም ለቃል ሆነ መራብ መጠማት መያዝ መዳሰስ መድከም መተኛት ሕማም ሞት ከመፍረስ እና ከመበስበስ ውጭ የቃል ገንዘቡ ሆነ።
" እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል "" የቃል የሆነው ሁሉ ለሥጋ ሆነ ለሥጋ የሆነው ሁሉ ለቃል ሆነ "እንዲል ቅዱስ ቄርሎስ።

ዘጠኝ ወር በማህፀነ ማርያም አድሮ በህቱም ድንግልና ተጸንሶ በህቱም ድንግልና ተወለደ ፍጹም ሰው ሆኗልና አምላክ ነኝ እና እለቱን ተፀንሼ እለቱን ልወለድ አላለም ግእዘ ሕጻናትን ጠብቆ የሰውነትን ሥርዓት አክብሮ ከኀጢአት በቀር ፍጹም ሰው ሆነ " "ወኮነ ሰብአ ፍጹመ ዘእንበለ ኃጢአት ባህቲታ" ከኃጢአት በቀር ፍጹም ሰው ሆነ።
ሰው ሆነ ሲባል ተለውጦ አይደለም።

1_ያለ መለወጥ /እንበለ ውላጤ/
ቃል ሥጋ ኮነ ሲባል ተለውጦ ሳይሆን ሥጋን ተዋህዶ ነው። ውላጤ የለበትም።
<u>ለምሳሌ፡</u>
1.1- "የሎጥ ሚስት ወደኋላዋ ተመለከተች የጨው ሀውልትም ሆነች"ዘፍ 19፡26 ተለወጠች ማለት ነው። ቃል ሥጋ ሆነ ሲባል ግን ሥጋን ተዋህዶ ፍጹም ሰው ሆነ አምላክነቱ ሳይለወጥ ሰውም ቢሆን አምላክ ነው። ሰው የሆነው ሳይለወጥ ነውና። "ሶበሰ አምላክ ባህቲቱ እምኢሀመ ወሶበሰ ሰብእ ባህቲቱ እምኢያድኅነ ካልአነ ሰብአ ሶበሰቀልዎ ወሞተ" "አምላክ ብቻ ቢሆን መከራ ባልተቀበለም ነበር ሰውም ብቻ ቢሆን ተሰቅሎ በሞተ ጊዜ ሰውን ባላዳነ ነበር" ሃይ አበ

ሰው ሆኗልና መከራ ተቀበለ አምላክ ነውና ዓለምን አዳነ ከዚህ አንጻር ሰው በመሆኑ አማኑኤል ኢየሱስ የሚሉ ስሞች ተሰጡት። አማኑኤል ማለት ሰው የሆነ አምላክ ፡ ኢየሱስ ማለት ደግሞ ወገኖቹን የሚያድን ማለት ነውና። እነዚህ ስሞች አምላክ ሰው ሰው አምላክ መሆኑን የሚያስረዱ ትስብዕት ከመለኮት መለኮት ከትስብዕት አንድ መሆኑን የሚገልጡ ናቸው።

## 1.2_የሙሴ በትር እባብ ሆነች

ይህም ውሳጤን የሚያሳይ ነው ሙሴ በትሩን ሲጥል እባብ ሆነች ሲያነሳት በትር ሆነች ተለወጠች ማለት ነው። አምላክ ሰው ሆነ ሲባልግን መለወጥ የለበትምና ያለመለወጥ ምሉዕ ተወሰነ ውሱንነቱን ሳይለቅ ውሱኑ ሥጋ ሞላ ውሱንነቱን ሳይለቅ ቃል ሥጋን ተዋህዶ ሳይለወጥ ሰው ሆነ ሥጋም ሳይለወጥ አምላክ ሆነ ምንታዌ ጠፋ አንድነት ጸና "እስመ ተዋሕዶ አዕተታ ለምንታዌ" "ተዋሕዶ ሁለትነትን አጠፋት/አጥፍቷልና" አንድነት አፀናት ከዚህ የተነሳ መለኮት እና ሥጋ ተዋሕደው አምላክ የሆነ ሰው ሰው የሆነ አምላክ ተባለ።

ኢየሱስ መጣ አማኑኤል ተወለደ እየተባለ ይነገራል አንድ ነውና።

## 1.3_የቃና ዘገሊላ ውሃ

የቃና ዘገሊላ ውሃ የወይን ጠጅ ሆነ ዮሐ 2፡1 ሲባል ቀድሞ ውሃ ነው ተለውጦ የወይን ጠጅ ኆኗል።

ቃል ሥጋ ሆነ ሲባል ግን ያለመለወጥ ነው። ውሳጤ አይስማማውምና

"አንሰ አምላክ ዘኢይትዌለጥ" "እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም" እንዲል ሚል 3፡6

## 1.4-የግብጻውያን ውሃ

ሙሴ በግብጽ ተአምራት ሲያደርግ "ወረሰየ ማዮሙ ደመ" "ውሃቸውን ደም አደረገ"

ማለት ለወጠው ማለት ነው። አካላዊ ቃል ግን ሰው የሆነው ያለመለወጥ ነው መለወጥ የለበትም።

"ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትማልም ወዮም ወክመ ውእቱ እስከ ለዓለም""ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬም መቼም ያው ነው" ዕብ 3፡

## 2_እንበለ ሚጠት /ያለመመለስ/

አካላዊ ቃል ሰው ሆነ ስንል እንበለ ሚጠት ነው። የሙሴ በትር ሲጣል እባብ ሆነ ሲያነሳት ግን በትር ሆነች። ተመለሰች ማለት ነው። ሥጋና ቃል ከተዋሕዶ በኋላ መመለስ የለባቸውም። አንድ ሆነው በአንድ ስም ጸንቶ መኖር ነው እንጂ።

## 3_እንበለ ቡአዴ /ያለመለያየት/ እንበለ ፍልጠት

ቃል እና ሥጋ ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት የለባቸውም። ተዋሕዶው የባሕርይ ነውና ።

## 4_እንበለ ቱሳሔ /ያለመቀላቀል/ መቀላቀል የለበትም

ቱሳሔ መቀላቀል ማለት ሲሆን የተቀላቀለ መለያየት ይችላል። ይህ የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ግን ፍጹሙ ተዋሕዶ በመሆኑ መቀላቀል የለበትም።

## 5_ሕድረት /ማደር/

ቃልና ሥጋ ሲዋሐዱ አንዱ በአንዱ ማደር የለባቸውም የተዋሕዶ እንጂ። ይህን ተዋሕዶ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በእሳት እና በብረት ተዋሕዶ መስለውታል፡

"ከመተዋሕዶተ ሐጺን ምስለ እሳት ወብርሃን ምስለ ዓይን ወሰሚአ ምስለ እዝን" "እሳት ከብረት ጋር

ሲቀላቀል ዓይንም ከብርሃን ጋር መስማት ከጆሮ ጋር እንዲስማማ ተስማምቶ ተዋሕዷል" እሳት ከብረቱ ጋር በተዋሐደ ጊዜ ብረቱ ፍጹም እሳቱን ይሆናል ፡ የእሳቱን ገንዘብ ገንዘብ ያደርጋል እሳቱም የብረቱን ሙሉ አካል ተዋህዶ ይታያል። ይህ እሳቱ ይህ ብረቱ ብለን ልንለየው አንችልም፡ ፍጹም ተዋህዷልና። የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ እንዲህ መለያየት የሌለበት ነው።

በሌላ መልኩ የቃልና  የሥጋ ተዋሕዶ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ተዋሕዶ ነው። እነርሱም ይህ ሥጋ ይህ ነፍስ ብለን መለየት እንዳይቻለን የቃል እና የሥጋን ተዋሕዶም መለየት አንችልም። ፍጹም ተዋሕዶ ነውና። ይህ ምሳሌ ግን ምሳሌ ዘየሀጽጽ መሆኑን አንርሳ። ከዚህ የተነሳ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ከሁለት ፈቃድ አንድ ከሁለት ግብር አንድ ግብር ሆነ ብለን እናምናለን ወልደ አብ ወልደ ማርያም እያልን እንጠራዋለን።

ማረን ይቅር በለን እንለዋለን እንጂ ማሩን ይቅር በሉን አንልም። ሁለትነት በተዋሕዶ  ተጣፍቶ  አንድነት ፀንቷልና።
"ሆረ ኢየሱስ በትፍስህት ውስተ ከብካብ" "ኢየሱስ ወደ ሠርግ ቤት ሄደ" "ኢየሱስ ከአልአዛር ቤት ገባ" ይባላል።

ይህን ተዋሕዶ መረዳት ያልቻሉ መለካውያን /ካቶሊካውያን/ ሥግው ቃልን ከሁለት ይከፍሉታል "መለኮት ይገብር ግብረ መለኮት ወትስብዕት ይገብር ግብረ ትስብዕት" "መለኮት የመለኮትን ሥራ ይሰራል ትስብዕትም የሰውነትን ሥራ ይሰራል" ይላሉ። ይህም ማለት መለኮት ድውይ ይፈውሳል ሙት ያስነሳል፡ እውር ያበራል ጎባጣ ያቀናል። ሥጋ ደግሞ ይተኛል ይራባል ይጠማል ኤሎሄ ኤሎሄ እያለ ይጸልያል?  ይላሉ። ይህ ግን ስህተት ነው።

ይህን በእኛ መረዳት ይቻላል፡ ጾም ስንጾም ግብሩ የነፍስ ቢሆንም ነፍስ ብቻዋን አትጾምም፡ ሥጋም ከምግብ ይከለከላል ነፍስና ሥጋ ተዋሕደዋልና። ቃልና ሥጋም ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት የለባቸውም። አንድ ግብር ናቸው። መለኮት በሥጋ ደከመ ተራበ ተጠማ ይባላል።
ሥጋማ ቢደክም ምን ያስደንቃል ?  ጥንቱንስ ድካም ገንዘቡ አይደለ?  የማይደክመው መለኮት በሥጋ ደከመ የማይጨበጠው ተዳሰሰ የማይሞተው ሞተ። መለኮትስ ድውይ ቢፈውስ ሙት ቢያስነሳ ምን ያስደንቃል ? የባሕርይ ገንዘቡ አይደለምን ?  ደካማው ሥጋ አምላክ ሆኖ የአምላክነትን ሥራ ሲሰራ ነው እንጂ ድንቁ?
"ምራቅም እንትፍ አለ በምራቁም የእውሩን ዓይን ቀባ" ዮሐ 9፡6
የቃል ምራቅ የለውም፡ የሥጋ ገንዘብ ነውና። "በምራቁ" የሚለው ቃል የሚገልጠው መለኮት ብቻ እውሩን ያበራው ዓልዓዛርን ከመቃብር የጠራው ሰው የሆነው አንድ አምላክ ነው።

ይህ የአምላክ ሰው የሰው አምላክ መሆን ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል። ይህንን አምኖ መቀበል ረቂቁ ግዙፍ ግዙፉ ረቂቅ ዳካማው ብርቱ ብርቱው ደካማ ውሱኑ ምሉዕ ምሉዑ ውሱን እንዴት ሊሆን ቻለ ሳይሉ ሳይጠራጠሩ መቀበል ነው። ይግለጥልን። ምሥጢር ያሰኘውም ይህ ሁኔታው ነው። በዚህ ድንቅ ተዋሕዶ በቤተልሄም ተወለደ በናዝሬት አደገ ተአምራትን አደረገ። ተጠመቀ አስተማረ በምድር ተመላለሰ"አንሶሰወ ገሀደ

ወአስተርአየ ከመ ሰብዕ"“በምድር ተመላለሰ ሰው እንደመሆኑ አደገ” ዲዮስቆሮስ።
ይህ ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል።

## 2.3 ምሥጢረ ጥምቀት

በምሥጢረ ሥጋዌ ሰው የሆነው አደገ ያልነው አምላክ በዮርዳኖስ ራሱን የገለጠበት በሩን ከፍቶ ለምዕመናን ያሳየበት ምሥጢረ ጥምቀት ነው። ጥምቀት አጥመቀ አጠመቀ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙ መጠመቅ መወለድ መታጠብ ማለት ነው፡
ጥምቀት በሁለት ክፍል ይከፈላል

### 2.3.1 የጌታችን ጥምቀት

ክብር ይግባውና ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በሠላሳ ዓመቱ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ አንድነቱን ሦስትነቱን ለመግለጥ ትህትናውን ለማስተማር ለአርአያነት ትንቢተ ነቢያትን ለመፈጸም ማያትን ለመቀደስ ዮርዳኖስን ብርህት ማኅፀን ለማድረግ ተጠምቋል።

በዚህ ጥምቀቱ አንድነቱን ሦስትነቱን ገለጠ፡ ትህትናውን አሳየን ፡ እርሱን አብነት አድርገን እንጠመቅ ዘንድ አርአያ ሆነን ዮርዳኖስን ቀደሰልን።

ከዚህ በተጨማሪ ጌታችን የተጠመቀበት ዋና ምክንያት የዕዳ ደብዳቤያችንን ይደመስስ ዘንድ ነው። “ወደምሰሰ ለነ መጽሐፈ እዳነ” እንዲል “የእዳ ደብዳቤያችንን ደመሰሰልን” ይህ የጌታችን ጥምቀት በዮርዳኖስ እንዲከናወን ትንቢት ተነግሯል ምሳሌ ተመስሏል ”ባሕር አየች ሸሸች ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ “ ”ምንተ ኮንኪ ባሕር ዘጎየይኪ ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባዕከ ድህሬከ“ ”ባሕር ምን ሆነሽ ነው የሸሸሽ ? አንቺስ ዮርዳኖስ ለምን ወደኋላሽ ተመለስሽ ? “ ማቴ
” ርእዩከ ማያት እግዚኦ ርዕዩከ ማያት ወፈርሑ “አቤቱ ውሆች አዩህ ፈሩህ “መዝ 76፡16 ፤ 113፡ 3_5
ይህ ትንቢት እንዲፈጸም በዮርዳኖስ ተጠመቀ።

**ምሳሌ**

ኤልሳዕ ደቀመዛሙርቱ በብዙ ጊዜ ”ፀበበነ ማህደር ንዑ ግዝም እፀወ ወንህንጽ ካልአ ማህደረ“ ”ቤት ጠበበን እንጨት ቆርጠን ሌላ ቤት እንስራ ባሉት ጊዜ“ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ይዟቸው ወረደ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንጨት ሲቆርጥ ምሳሩ ከእጀታው ወልቆ ከባሕሩ ገባበት፡ ”ዝኒ ህቡይ እግዚእየ“ ያውም የተውሶ ጠፋ ተጨረሶ አለው፡ ኤልሳዕ ቅርፍተ ዕፅ አመሳቅሎ ጣለበት፡ መጥለቅ የማይገባው ቅርፍተ ዕፅ ጠልቆ መጥለቅ የሚገባውን ብረት አወጣው።

እንዲሁም መሞት የማይገባው ጌታ ሞቶ አዳምን የማዳኑ ምሳሌ ነው። ጌታችን ሞቱ አዳምን ከማዳኑ በፊት ተጠምቆ የእዳ ደብዳቤያችንን ደምስሷልና።

ይህ የጌታ ጥምቀት እርሱን ከመጥቀም በታች ነው። ጥቅሙ ለእኛ ነው እርሱ እጸድቅ አይል ጻድቅ /የባህርይ አምላክ/ እከብር አይል ክቡር አይጠቅመውም ለእኛ ነው ጥቅሙ። ይህን ይፈጽም ዘንድ በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠመቀ።

" አሜሃ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይጠመቅ እም ኀበ ዮሐንስ ወዮሐንስሰ አበዮ ወከልአ እንዘይብል አንሰ እፈቅድ እምኀቤከ እጠመቅ ወአንተኑ ትመጽእ ኀቤየ "" ያን ጊዜ ጌታ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን አይሆንም አለው ከለከለው እኔ በአንተ ልጠመቅ ይገባኛል እንጂ አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን ? "" ህድግ ምእረሰ ? ወይደልወነ ከመንፈጽም ኩሉ ጽድቀ" "አንድ ጊዜ ተወው ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናል"። ጽድቅ ትንቢተ ነቢያት ነው።

" እስመ ከመዝ ተድላ ውእቱ ለነ "" ይህ ለእኔም ላንተም ተድላ ደስታችን ነው አንተ መጥምቀ መለኮት ተብለህ ልዕልናህ ሲነገር ይኖራል እኔም በባሪያው እጅ ተጠመቀ ተብሎ ትህትናዬ ሲነገር ይኖራል" አለው።

ዮሐንስም ባዕደሰ አጠምቅ በስምከ ወበስመ መኑ አጠምቅ ኪያከ" ሌላውን በአንተ ሥም አጠምቀዋለሁ አንተን በማን ስም ላጥምቅህ "ወልዱ ለአብ ከሳቴ ብርሃን ተሣሃለነ" "ብርሃን የምትገልጥ የቡሩክ አብ ልጅ እያልክ አጥምቀኝ" አለው
በዚህ መሰረት ጌታ በባሪያው በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ተጠመቀ። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየ" ማቴ 3፡17

**ጌታ ለምን በውሃ ተጠመቀ ?**
ውሃ ለመአት እንጂ ልምሕረት አልተፈጠረም የሚል አመለካከት ያላቸው ሰዎች ነበሩና ለምሕረት እንደተፈጠረ ለማስረዳት።
ውሃ ለሁሉ ይገኛል ሁሉ በሚያገኘው "ማይሰ ርኩብ ለኩሉ" እንዲል አብጥሊስ
እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል፡ እናንተም ብትጠመቁ ገነት መንግስተ ሰማያት ትገባላችሁ ሲል።
ውሃ ከእድፍ ያነጻል ጥምቀት ከኃጢአት ያነጻልና።

### 2.3.2 የሰውልጅ ጥምቀት

የሰው ልጆች ጌታን አብነት አድርገን የምንጠመቀው ጥምቀት ሁለተኛው ነው፡
"እነዝሀክሙ በማይ ቅዱስ ከመትንጽሁ እምርኩስክሙ" "ንጹህ ውሃ እረጭባችኋለሁ ከርኩሰታችሁም ትጠራላችሁ" ሕዝ 36፡25 እንዲል የሰው ልጅ ያጣውን ልጅነት ገንዘብ ለማድረግ ይጠመቅ ዘንድ ግድ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትን በተግባር አሳይቶ በግዝረተ ሥጋ ተክቶ ለሰው ልጆች ሰጠን፡ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማህፀነ ዮርዳኖስ እንወለድ ዘንድ።

የሰው ልጅ ረቂቅ ልደትን ከእግዚአብሔር ተወልዶ ሰይጣንን ክዶ የመንግስተ ሰማያት ወራሽ የስሙ ቀዳሽ

የሚሆነው በጥምቀት ነው ጌታችን ይህን ፅኑ መመሪያ የቃልኪዳን ምልክት አድርጎ ሰጥቷል።

“ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን ወዘሰ ኢአምነ ወዘኢተጠምቀ ይደየን” “ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል” ማር 16፡16 ብሎ የመኑ ሁሉ መጠመቅ እንዳለባቸው አስተምሯል።

ጥምቀት መንግስተ ሰማያትን ለማግኘት ወሳኝ ነው። ጌታችን ለኒቆዲሞስ ይህን አስረግጦ ነግሮታል።
“አማን አማን እብለከ ዘኢተወልደ ዳግመ ኢይክል ርዕዮታ ለመንግሥተ እግዚአብሔር” “እውነት እውነት እልሀለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም” “ወይቤሎ ኒቆዲሞስ በእፎ ይክል ብዕሲ ዳግመ ተወልዶ እምድህረ ልሀቀ ይክልኑ በዊአ ወገቢአ ውስተ ከርሰ እሙ ወይትወለድ ዳግመ “ሰው ከሸመገለ በኋላ ወደ አባቱ አብራክ ተመልሶ ወደ እናቱ ማህጸን ገብቶ እንዴት ሊወለድ ይችላል ? “አማን አማን እብለከ ዘኢተወልደ ዳግመ እማይ ወመንፈስ ቅዱስ ኢይክል በዊኦ ውስተ መንግስተ ስማያት”” እውነት እውነት እልሀለሁ ሰው ዳግመኛ ከውሃ እና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ መንግስተ ሰማያት ሊገባ አይችልም” ብሎ ልደቱን እና መወለጃውን ቢነግረው ለኒቆዲሞስ አይቶት የማያውቅ በመሆኑ ኒቆዲሞስ በቀላሉ ሊረዳው አልቻለም። ወላጁ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሳ ልደቱ ረቂቅ ነውና፡ ኒቆዲሞስን ለማስረዳት ጌታችን እንዲህ ይለዋል፡

“እስመ በእንተ ዝንቱ ኢታንክር እስመ ሶበ እቤለከ ሀለወክሙ ትትወለዱ ዳግመ እስመ መንፈስ ኀበ ፈቀደ ይነፍህ ወቃሎ ትሰምእ ወኢተአምር እም ኀበ ይመጽእ ወነበዪ የሀውር ከማሁ ኩሉ ዘይትወለድ እም መንፈስ ቅዱስ” “ዳግመኛ ትወለዳላችሁ ስላልኩህ አታድንቅ፡ ነፋስ ወደ ወደደው ይነፍሳል ድምፁን ትሰማለህ ከየት እንደ መጣ ወደየት እንደሚሄድ ግን አታውቅም። ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱት ልደትም እንደዚህ ነው” ዮሐ 3፡3_9

እዚህ ላይ ልደቱ ረቂቅ መሆኑን አስረድቷል። ሰው እንኳን ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለደውን ረቂቅ ልደት ከእናት ከአባቱ የተወለደውን ሥጋዊ ልደት እናት አባቱ ያውቁታል ይነግሩታል እንጂ እርሱ እንዳያውቀው እኛም ከእግዚአብሔር የምንወለደውን ልደት ሥላሴ ያውቁታል እንጂ እኛ አናውቀውም።

መንፈስ ወደወደደው ይነፍሳል ማለት መንፈሰ ረድኤት በወደደው ያድራል፡ ማለት ሀብተ ሙሴ በኢያሱ፡ ሀብተ ኤልያስ በኤልሳዕ ሲያድር አይታይም አድሮ ባሕር ሲከፍል ሙት ሲያስነሳ ተአምራት ሲያደርግ ነው እንጂ የሚታይ ።

መንፈሰ ልደትም ሲሰጥ አይታይም በሰዎች አድሮ ድውይ ሲፈውስ ተአምራት ሲያደርግ ይታያልና። ይህ ጥምቀት አምነን ፈጣሪያችንን የምንቀበልበት የእግዚአብሔር ልጆች የምንሆንበት ነው።

“ኀበ እሊአሁ መጽአ ወእሊአሁሰ ኢተወከፍዎ ወለእሉሰ ተወክፍዎ ወሐቦሙ ሥልጣነ ወልደ እግዚአብሔር ይኩኑ ለእለ አምኑ በስሙ እለ ኢኮኑ ዘሥጋ ወደም ወኢ እም ብእሲ ወብእሲት አላ እምእግዚአብሔር ተወለዱ” “የእርሱ ወደሆኑት መጣ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት

ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ አልተወለዱም ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" ዮሐ 1፡12

በዚህ መሰረት ጥምቀት የሰው ልጆች ከልደተ ሥጋ እጅግ የከበረ ልደትን የሚወለዱበት ልደተ ሥጋን ያይደለ ልደተ መንፈስን ገንዘብ የሚያደርጉበት ነው፡፡

ለቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታቸው የተሰጣቸው ሌላው መመሪያ ይኸው የጥምቀት ጉዳይ ነው፡
"ሑሩ ወመሐሩ ኩሎ አሕዛበ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና አህዛብን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው" ማቴ 28፡19
ስለዚህ ጥምቀት ለሰው ልጆች ጾታ የማይለይ ትልቅ ትንሽ የማይል የሰውን ልጅ ማዕከል ያደረገ ምሥጢር ነው፡፡
በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋ የሚያሰጥ ነው፡፡ ካህኑ ውሃውን በብርት አድርጎ ሥርዓቱን ሲፈጽም ተጠማቂው ሲፈጸምለት ይታያል የማይታይ ረቂቅ ልደት በዚህ አማካኝነት ያገኛል፡፡

<u>የጥምቀት ምሳሌዎች</u>

**1_ማየ አይህ**

ማየ አይህ ዓለም በኃጢአት እና በመርገም እግዚአብሔርን በማሳዘኑ የጥፋት ውሃ ዓለምን ከኃጢአት አጥፏታል፡፡ ጥምቀትም በፍዳ እና በመርገም ተይዞ የነበረው የሰው ልጅ ያጣውን ልጅነት ያገኝበት ዘንድ የተሰጠ ነውና፡፡
"ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግስት በኖህ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል" 1ጴጥ 3፡20

የሚከተሉትን ቁም ነገሮች መመልከት ይገባል

- ጥምቀት _ለድኅነት
- መርከብ_ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓቱ የሚፈጸምበት ያድናል፡፡
- በመርከቡ ውስጥ የዳኑ ሰዎች ተጠምቀው ድኅነት የሚያገኙ ሰዎች ምሳሌ ነው

**2_የእስራኤል ኤርትራን እና ዮርዳኖስን መሻገር**

"ወንድሞቻችን ይህንን ልታውቁ እንወዳለን አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ" 1ቆሮ 10፡1

ልብ ማለት ይገባል፡ ዮርዳኖስ የጥምቀት እስራኤል የምእመናን ምሳሌ ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ሙሴ ሕዝቡን ወደ ምድረ ርስት መርቷል ክርስቶስም ባሕረ ሲኦልን ከፍሎ ሕዝቡን ወደ ገነት ወደ መንግስተ ሰማያት አስገብቷል፡፡
ሕዝቡ ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ ተጠመቁ ምዕመናን ከክርስቶስ ጋር ህብረት ይኖራቸው ዘንድ ይጠመቃሉ፡፡

**3_ጥምቀተ ዮሐንስ**

“አንሰ አጠምቀክሙ በማይ ለንስሐ ወማእከሌክሙ ሀሎ ዘኢተአምርዎ አንትሙ ወውእቱ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት” እኔ ለንስሐ በውሃ አጠምቃችኋለሁ እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ አለ እርሱ በእሳት እና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል “ማቴ 3፡11 ማር 1፡8 ሉቃ 3፡16 ዮሐ 1፡33 የምሳሌዎች መደምደሚያ የሚከተለው ነው፡፡

**4_የክርስቶስ ሞት**

የክርስቶስ ሞት የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ ምክንያቱ ጌታችን ሞቶ ሦስት መአልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ብርሃነ መለኮቱን ገልጦ እንደተነሳ እኛም ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለን ተጠምቀን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን የሥላሴን ልጅነት አግኝተን ከኃጢአት ባርነት ከዲያቢሎስ ቁራኝነት ነጻ እንሆናለንና፡፡

” ወበ ጥምቀተ ክርስትና ቅድስት ይከውን ሰብእ አግአዚ ፍጹመ እምቅኔተ ኃጢአት ወእምስልጣነ ዲያቢሎስ ወአጋንንቲሁ ፀዋጋን ወይከውን አምሳለ ልደቱ ለክርስቶስ ዘተወልደ እንበለ ፍትወት “

ቅድስት በሆነች የክርስትና ጥምቀት ሰው ከኃጢአት ባርነት ከዲያቢሎስ ቁራኝነት ነጻ ይሆናል ክፉ ከሆኑ ከሠራዊቱም ያለ ዘርአ ብእሲ እንደተወለደ እንደ ክርስቶስ ያለ ልደት ይወለዳል” እንዳለ አብጥሊስ
ከዚህ የተነሳ ጌታችን ”ትክሉኑ ሰትየ ጽዋዕ ዘአነ እሰቲ ወጥምቀትየኒ ትጠመቁኑ“ “እኔ የምጠጣውን ጽዋዕ ልትጠጡ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁ” ማቴ 19፡22 ይህ ማለት የምሞተውን ሞት ማለቱ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡
ስለዚህ ጥምቀት የሞቱ ምሳሌ ነው እንላለን፡፡ እንደመሞት ከዓለም ግብር እንለይበታለን ፡ እንደመቀበር ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እንልበታለን እንደመነሳት ብርሃን ለብሰን ብርሃን ተጎናጽፈን ልጅነትን አግኝተን እንወጣበታለን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን እናረጋግጥበታለን፡፡

ከብዙ በጥቂቱ ምሳሌዎችን ካየን የእኛ ጥምቀት እንዴት ይፈጸማል ? የሚሉትን በጥቂቱ እንመልከት፡

**1_ማየ ገቦ /ከጌታ ከቀኝ ጎኑ በሚፈስ ውሃ**
**2_ደመ ሰማዕታት /ሰማዕታት በደማቸው/**
**3_በአንብአ ንስሐ ይፈጸማል**
በእነዚህ በሦስቱ ልጅነት ይገኛል ጥምቀት ይፈጸማል፡፡ አንዱ መደበኛ ሁለቱ የችግር መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

**1_ማየ ገቦ /ከጌታ ከቀኝ ጎኑ በሚፈስ ውሃ**

በማየ ገቦ ያልነው ካህኑ ውሃውን በብርት አቅርቦ ልብሰ ተክህናውን ለብሶ በቁጥር 12 ካልተቻለ 7 ቢጠፋ 5 ልኡካን ይዞ ሥርዓቱን አድርሶ ውሃውን ሲባርከው በእለተ አርብ ከጌታ ቀኝ ጎን የፈሰሰ ማየገቦ ይሆናል፡፡ በዚህ ይፈጸማል፡፡ ያጠምቀዋል ሜሮን ይቀባዋል ሥጋወደሙን እለቱን ያቀብለዋል በዚህ መልኩ ይከናወናል፡፡

ይህም የሚከናወነው ፡

- በጠዋት _ሲመጡ / በአርባ እና በሰማንያ ቀናቸው
- በቀትር _ሲመጡ በጉልምስና ለመቱመጡ
- በሠርክ_በሽምግልና ለመጡ ይፈጸምላቸዋል
- ሁሉም ሥርዓት በአግባቡ የፈጸምላቸዋል፡፡
    - ያጠምቃቸዋል
    - ማዕተብ ያስርላቸዋል
    - በሜሮን ያትማቸዋል
    - ሥጋወደሙን ያቀብላቸዋል

**2_ደመ ሰማዕታት /ሰማዕታት በደማቸው/**

ሰማዕታት በክርስቶስ አምነው ከመጠመቃቸው በፊት በአላውያን ሰይፍ ቢቀጡ በደማቸው ልጅነት ያገኛሉ፡፡ "እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ ትችላላችሁን" ያለውን ፈጽመዋልና ማቴ 19፡22

**3_በአንብአ ንስሐ ይፈጸማል**

በአንብአ ንስሐ ያለውም አምነው ካህን አጥተው ለሚያለቅሱ ሰዎች የሚፈጸም ነው፡፡
"ብፁአን እለ ይላህው ይዕዜ እስመ እሙንቱ ይትፌስሑ ዛሬ የሚያለቅሱ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና" ያለውን ስለ ፈጸሙ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ልጅነት ያገኙ ሁሉ ተጠምቀዋል፡፡

<u>**ጥምቀት ለምን ?**</u>

**1-ክርስቶስን ለመምሰል /ለመተባበር/**

"ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር/በአምላክነት ክብሩ/ ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁ እኛ በአዲስ ሕይወት እንመላለስ ዘንድ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" ሮሜ 6፡3_6

**2_የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን**

"እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛ ከውሃ እና ከመንፈስ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያየት አይችልምና" ዮሐ 3፡3_8

"ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያው ለዘለዓለምም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ" 1ጴጥ 1፡23

"ነገር ግን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አድነን" ቲቶ 2፡4_6

**3_ለድኅነት**

"ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ማር 16፡16

ቅዱስ ጳውሎስንና ቅዱስ ጴጥሮስን የእስር ቤት ጠባቂ “ጌቶቼ ሆይ እድን ዘንድ ምን ላድርግ ? አላቸው እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እመን ትድናለህ እርሱ ከቤተሰቦቹ ጋር ተጠመቀ” ሐዋ 16፡30 1ጴጥ 3፡17

**ጥምቀት ለማን? በምን**

ጥምቀት ለሚያምኑ ሰዎች በእምነት ይሰጣል።

” ተነሳና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ አሁንስ ለምን ትዘገያለህ ? “ሐዋ 22፡17

“ጃንደረባውም እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ ምን ይከለክለኛል ? ብታምን ተፈቅዷል” ሐዋ 9፡17 8፡34

በዚህ መሰረት ለሚያምኑት የሚፈጸም ምሥጢር ነው ፡ ምሥጢረ ጥምቀት ምሥጢር የሚባለውም ውሃው ሲለወጥ አይታይምና፡ ከመንፈስ ቅዱስም ስንወለድ አይታይምና ነው።

ሰው በሃይማኖት ተጠምቆ ከእግዚአብሔር ተወልዶ ተአምራት ሲያደርግ በተግባር ይገለጣል እንጂ አይታይምና ምሥጢር ይባላል።

## 2.4 ምሥጢረ ቁርባን

ምሥጢረ ቁርባን አንድነቱን ሦስትነቱን ሥጋዌን አምኖ ለተጠመቀ የሚፈጸም የምሥጢራት ሁሉ መደምደሚያ ነው።ቢያምኑም ቢጠመቁም ሥጋውን መብላት ደሙን መጠጣት የግድ ያስፈልጋል።ይህ ቁርባን ከመስዋዕተ ኦሪት የተለየ የከበረ ነው።የብሉይ ኪዳን መስዋዕት ከእንሰሳት ወገን ነበር።የሚሰዋ ሟች በመሆኑ መስዋዕቱ ግዳጅ ፈፃሚ አልነበረም።"እስመ ብዙኃን አልህምት ሞቱ ወአልቦ ዘበቁአ ሞቶሙ ወዘክርስቶስሰ ዓለመ አድኀነ" "ብዙ ላሞች ተሰው መስዋዕታቸው ዓለምን ማዳን አልቻለም።የክርስቶስ ሞት ግን ዓለምን አዳነ" ለቀድሶተ ሥጋ ወነፍስ ነፍስና ሥጋ የሚቀድስ ገነት መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርስ ነው።ቁርባነ ወንጌል እንደ ኦሪት መስዋዕት የላሙ የበጉ የፍየሉ የርግቡ የዋኖሱ ቁርባን የእህሉ ነው።አሁን ያ በመቅረቱ ቁርባኑም መስዋቱም አንድ ነው።ካህኑ ህብስቱን በፃህል ወይኑን በጽዋ አቅርቦ አሀዱ አብ ቅዱስ አሀዱ ወልድ ቅዱስ አሀዱ ውእቱ መንፈስቅዱስ ብሎ በባርከው ጊዜ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት ሕብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ይሆናል።ቁርባን የሚባለው ይህ ነው።መስዋዕቱም እርሱ ነው።

**የመስዋዕተ ወንጌል ምሳሌዎች**

### 1. መስዋዕተ መልከ ጼዴቅ

አብርሃም ወደ እርሱ በእግዚአብሔር ተልኮ እንዲመጣ ባወቀ ጊዜ ሕብስተ አኮቴት ጽዋአ በረከት አዘጋጅቶ ተቀብሎታል።አብርሃም ለአራቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አምስቱን ነገስተ ኮሎዶጎሞርን ድል ነስቶ "በመዋዕልየኑ ትፌኑ ወልደከ ወሚመ ታርእየኒሁ ኪያሃ ሰዓተ ወኪያሃ እለተ አኮ ዘትሬኢ ኪያሃ ሰዓት ወኪያሃ ዕለተ ወባሕቱ ሁር እድወ ለዮርዳኖስ ወበህየ ትረክቦ ለመልከ ጼዴቅ ወውእቱ ያርእየከ ምስሌሃ" "በዘመኔ ልጅህን ትልካለህን? ወይስ ያችን ቀን እና ሰዓቷን ታሳየኛለህን? ቀኗን አታይም ሰዓቷንም ነገር ግን ዮርዳኖስን ተሻግረህ ሂድ በዚያም መልከ ጼዴቅን ታገኘዋለህ እርሱም ምሳሌውን ያሳይሃል አለው።" ዘፍ 14፡18

በታዘዘው መሰረት አብርሃም ዮርዳኖስን ተሻግሮ መልከ ጼዴቅን አግኝቶ ህብስተ በረከቱን በልቶ ጽዋ በረከቱን ጠጥቶ ተባርኮ ተመለሷል።አብርሃም የምእመናን መልከ ጼዴቅ የካህናት ህብስተ አኮቴት ጽዋ በረከት የሥጋና የደሙ ምሳሌ ነው።አብርሃም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሄዶ እንደተቀበለ ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ።ይህ ምሳሌ ኦሪት ከመሰራቱ መስዋዕተ ኦሪት ከመስዋዕቱ አስቀደሞ መሆኑን ልብ ይሏል።ከመስዋዕተ ኦሪት አስቀድሞ መስዋዕተ ወንጌል ታይታለች በምሳሌው።

## 2.መስዋዕተ አብረሃም

አብርሃም በመስዋዕቱ በሞርያ (ቀራንዮ) ያቀረበው ልጁ ወይም በልጁ ምትክ የሰዋው በግ ነው። "ሱዐ ሊተ ይስሓቅሃ ወልደከ ዘታፈቅር" የምትወደውን ልጅህን ይስሓቅን ሰዋልኝ ብሎ እግዚአብሔር አብርሃምን ባዘዘው ጊዜ ልዋል ልደር ከቤተሰቤ ልምከር ሳይል "ወተንስኣ አብርሃም በሌሊት ወረሀነ አድጎ ወነስአ ደቂቆ"አብርሃም በሌሊት አህያውን ጭኖ ልጁ ይስሃቅን ሁለቱን አገልጋዮች አስከትሎ "ወሆረ ምህዋረ ሰሉስ" የሶስት ቀን መንገድ ሄዶ በሞሪያ ተራራ ላይ የብርሃን አምድ ሲጠቅሰው አይቶ እዚህ ነው ሰዋው ያለኝ ብሎ ሁለቱን አገልጋዮቹን ከእግረ ደብረ "አነ ወልድየ ሰጊደነ ንገብዕ " እኔና ልጄ ሰግደን እንመለሳለን ብሎ ይስሐቅን እንጨቱን አሸክሞ ይዞት ወጣ።መሰዊያውን አዘጋጅቶ ሊሰዋው ሲል "ኢትደይ እዴከ ላዕለ ወልድከ ይስሃቅ" በልጅህ በይሐቅ ላይ እጅህን አታንሳ የሚል ቃል በመስማቱ ቀና ሲል በዕፀ ሳቤቅ የታሰረ ቀንዱ ያልከረከረ ፀጉሩ ያላረረ በግ አይቶ ልጁን ፈትቶ በጉን ሰውቶ ተመልሷል።

አብርሃም የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ - አብርሃም ልጁን ለመስዋዕት እንደሰጠ አብም አንድ ልጁን ሰጥቷልና

ይስሃቅ የእግዚአብሔር ወልድ - ይስሃቅ እንደታዘዘ ወልድም ዓለምን ለማዳን ታዝዟልና

እንጨቱ የዕፀ መስቀል - ይስሃቅ እንጨቱን እንደተሸከመ ክርስቶስም መስቀሉን ተሸክሞልና

ሁለቱ አገልጋዮች የፈያታዊ ዘየማንና ዘፀጋም - ሁለቱ አገልጋዮች እንዳልተሸከሙ ፈያትም አልተሸከሙም

በሌላ መልኩ

ይስሃቅ የዚህ ዓለም

በግ የጌታ ምሳሌ ነው

ያ በግ ይስሃቅን ቤዛ ሆኖ እንዳዳነው ይህን ዓለም ክርስቶስ ቤዛ ሆኖ አድኖታልና። መስዋዕቱ የዓለሙን ኃጥያት የሚያስወግድ "እነሆ የእግዚአብሔር በግ" ዮሐ 1:29

## 3.እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ የሰውት መስዋዕት

እስራኤል ከግብፅ በወጡ ጊዜ በጉን ሰውተው ሥጋውን በልተው ደሙን ሞተ በኩር ያርቅላቸው ዘንድ የቤታቸውን መቃንና ጉበኑን ቀብተው ነበር።በጉን ሲበሉ የተሰጠ መመሪያ ነበር።

- . ለነገ አታስቀሩ

- . ጥብሱን ብሉ
- . ብርንዶውን አትብሉ
- . ጫማ አዝባችሁ ብሉት
- . ኩፌት ደፍታችሁ
- . እየቸኮላችሁ
- . መፃፃ (አልኮል)ጨምሩበት
- . ተሰብስባችሁ ብሉት ዘፀ 12:1-15

እነዚህ በጉ ሲሰዋ የተሰጡት መመሪያዎች በውስጣቸው ያዘሉት ምሥጢር አሁን ያለውን የሥጋውንና የደሙን ነው::ምሳሌ ሁልጊዜ በውስጡ ወርቅ አለውና ትርጉም ያሻዋል::

- ለነገ አታስቀሩ- መስዋዕት ተሰውቶ ለነገ ማደር የለበትም
- -ጥብሱን ብሉ- ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው ብላችሁ ተቀበሉት ሲል ነው:
- -ብርንዶውን አትብሉ- ሩቅ ብዕሲ ነው ብላችሁ ሥጋውን ደሙን አትቀበሉ
- -ጫማ አርጋችሁ-ምግባረ ወንጌልን ይዛችሁ ተቀበሉ "ተሰኢነክሙ ኃይለ ወንጌል"እንዲል
- -ኩፌት ደፍታችሁ- አክሊለ ሶኩን እያሰባችሁ
- -እየቸኮላችሁ- እለተ ሞታችሁን እያሰባችሁ
- -መፃፃ--የሰራችሁትን መራራ ኃጥያት እያሰባችሁ

-በሎታ ይዛችሁ-ለእኔ ሲል ራሱን በዘንግ ተመቷል እያላችሁ መከራውን በማሰብ ማለት ነው:

<u>ትንቢት</u>

**ምሳሌ እንደተመሰለ ሁሉ ትንቢት ተነግሯል**

"አስተዳለወ መስዋዕቶ ወቀደሶሙ ለህሩያኒሁ" መስዋዕቱን አዘጋጀ የተመረጡትንም ቀደሳቸው (ሶፎ 1:7) "እምፍሬ ሥርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝሀ" -ከስንዴ ፍሬ ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ::" መዝ 4:6 "ምስለ ቁቅሀ ሥርናይ ወደመአስካል ስትዩ ወይነ-ከሥንዴ እሸት ጋር ከወይኑም ደም ያለውን ጠጅ ጠጣህ"ዘዳ32:14

"ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንት ውእቱ ሕይወቱ ሕዳጠ ወይነ ቶስህ በእንተ ህማመ ከብድከ ወበእንተ ደዌከ ዘዘልፍ " ወይን የማይጠጣ ህይወቱ ምንድነው-ስለህመምህ ይልቁንም ስለሆድህ ህመም ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ" የሚሉት የቅዱሳን መጻህፍት ክፍሎች ሥጋው ደሙ ከስንዴና ከወይን እንደሚዘጋጅ በትንቢትም በምሥጢርም የተነሩ ናቸው:: ይህም ይፈጸም ዘንድ::

በዕለተ ሐሙስ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ህብስቱን ባረከ ደሙን ቀደሰ እለተ ዓርብ የሚቆረሰው ሥጋዬ ይህ ነው::የሚፈሰው ደሜም ይህ ነው::ህይወት ይሆናችሁ ዘንድ ብሉ ጠጡ ብሎ በመስጠት ምሳሌውን ተርጉሞ ትንቢቱን ፈጽሞ መስዋዕተ ኦሪትን ሽሮ መስዋዕተ ወንጌሉን አክብሮ ምሥጢረ ቁርባንን አስተማረ::

"ወእንዘ ይበልዑ ነስአ ህብስተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢየሁ ወይቤሎሙ ንስዑ ብልዑ ዝህብስት ሥጋየ ውእቱ ወነስአ ጽዋዐነ አዕኮተ ወወሐቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንስዑ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ

ዘይትከአው ለቤዛ ብዙኃን ወለህድገተ ኃጢአት- ሲበሉም እንጀራውን አንስቶ ባረከ ለደቀ መዛሙርቱም ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህ አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ለብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈሰው የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡" ማቴ 26:26 ማር 14:22 ሉቃ 22:18 1ቆሮ 11:23

በዚህ መሰረት ይህን ምሥጢር ለሚገባቸው ለሐዋርያት አሳየ:: ለቤተክርስቲያን በቅዱሳን ሐዋርያት የተሰጠ የተገለጠ ምሥጢር ነው ምሥጢረ ቁርባን::የክርስቲያኖች ህይወት ያለዚህ ሊሆን አይችልም ይህን ምሥጢር መካፈል መቀበል ያሻቸዋል::

ጌታችን በተግባር ከማሳየቱ አስቀድሞ በሰፊው አስተምሯል:: ስለምስጢረ ቁርባን "አበዊነሰ መና በልዑ በገዳም:: ወአውስአ እግዚእነ ኢየሱስ አማን አማን እብለክሙ አኮ ሙሴ ዘወሐበክሙ ውዕተ ኅብስተ ኣላ አቡየ ወሐበክሙ ህብስተ ጽድቅ እምሰማይ" ይህን እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም ሰማያዊ አባቴ ሰማያዊ እንጀራ ሰጣችሁ እንጂ ይህውም የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ ነው::

አነ ውዕቱ ሕብስተ ሕይወት- ኢየሱስ እንዲህ አላቸው የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔም የሚያምን ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም:: (ዮሐ 6:31-32)

አነ ውዕቱ ሕብስተ ሕይወት አበዊክሙሰ በልዑ በገዳም ወሞቱ አነ ውዕቱ ሕብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ከመ ኩሉ ዘበልዐ እምኔሁ ኢይመውት ኣላ የሐዩ ለዓለም- እውነት እውነት እላችኂላሁ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ:: ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል እኔም ለዘላለም የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው::

እንግዲህ አይሁድ ይህ ሰው ሥጋውን እንበላ ዘንድ እንዴት ይሰጠን ዘንድ ይችላል ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው እውነት እውነት እላችኂለሁ የወልደ እጓለመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ:: ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ::(ዮሐ 6:47-59)::

ይህን አስተምሮ በተግባር ለሐዋርያት አሳያቸው:: ምሥጢሩን ጀመረው ማለት ነው:: ስለዚህ ወደ ክርስትና የሚመጣ ሁሉ ኃጢአቱ ይሰረይለት ጸጋው ይበዛለት ዘንድ ይህን ምሥጢር ይካፈላል:: በዚህም ከክርስቶስ ጋር ይተባበራል:: እስራኤል ሙሴን ይተባበሩት ዘንድ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ:: ምዕመናንም ክርስቶስን ይተባበሩት ዘንድ ሥጋውን ይበላሉ ደሙን ይጠጣሉ በዚህም ስርየተ ኃጢአት ያገኛሉ::

"ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኩሉ ኃጣውኢነ - የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ያነጻናል:: 1ኛ ዮሐ1:8 ምልክታችን ማህተማችን ነው:: "እነዚህ ከታላቁ መከራ (ሰማዕትነት )በበጉ ደም አጥበው ልብሳቸውን (ሰውነታቸውን ) አነጹ" ራዕ 7:15 በዚህም መሰረት ካህኑ ህብስቱን ወደ ሥጋው ወይኑን ወደ ደሙ ይለውጠዋል ይህን ይሆን አይሆን ሳይሉ ሳይጠራጠሩ መቀበል ነው::

## 2.5 ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ይህ ምሥጢር መጨረሻቸው ነው:: የሰው የሃይማኖት መደምደሚያ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

- ሁሉን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን
- ከአብ በተወለደ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን
- ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን
- ሐዋሪያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን እናምናለን
- በአንዲት ጥምቀት እናምናለን

-የሙታንንም መነሳት ተስፋ እናደርጋለን ሰለስቱ ምዕት የሁሉ መደምደሚያ ይህ ተስፋ አዘል ምሥጢር ነው። ተስፋው የሚመጣው ህይወት ነው። ይህ አንድ ጊዜ ከተሰጠ የማይነሳ ካገኙት የማያጡት ከገቡ የማይወጡት ሐዘን ጭንቀት የሌለበት የሰው እኩል መሆን በትክክል የሚረጋገጥበት ትልቁ ትንሹን ዝቅ አድርጎ የማይመለከትበት የዚያ ህይወት በር መግቢያ ትንሳኤ ሙታን መነሳት ነው።

ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን በሁለት ይከፈላል

1. የጌታችን የመድሃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ የሰው ልጆችን ትንሣኤ ያበሰረ ሞትን የሻረ መቃብርን ያሳፈረ ትንሳኤ ነው።የሰዎች ተስፋ ትንሣኤው መሆኑ በግልጥ የታየበት ነው።እስከ አሁን እንደተመለከትነው አምላክ ሰው ሆነ ተወለደ አደገ ተጠመቀ የሰውን ልጅ ለማዳን በምድር ተመላለሰ ብለን ነበር።የዚህ ሁሉ ሥራ መከሩ ተንሣኤ ነው።ትንሣኤ ባይኖር ይሔኔ ጌታችን መወለዱ ማስተማሩ ዓለምን ማዳኑ በከርሰ መቃብር ማደሩ ሁሉም ተዘንግቶ ነበር። ተገልጦ ሲያስተምር ለመቀበል የተቸገሩት ሁሉ ያስደነገጠ የአጋንንትና የአይሁድ ልብ በመሸነፍ የተዋጠ ከስቅለቱ ማግስት የተደረገው ትንሣኤ ነው።ትንሣኤ የጌታችን የሰውነት ሥራ አክሊል ነው።ከአቤል ጀምሮ እስከክርስቶስ በሰው ልጅ ላይ አንዱ ሊባል ሌላኛው ሊቀበል ቃልኪዳን ገብተው የኖሩ ሞትና መቃብር የመስጠት የመቀበል እንጂ ይዞ አፍርሶ አበስብሶ ማስቀረታቸውን የሻረ ትንሣኤ ነው።ሞትን ያህል ጉልበታም መቃብርን ያህል አስከፊ ጠላቶችን ድል ነስቶ ሰው ሞትን እንዳይፈራ በመቃብር እንዳይደነግጥ ተስፋውን አለመለመው። ትንሣኤ በመቃብር በብዙ ሰዎች ታጅቦና ተከቦ ለብዙ ዘመናት እና ለረጅም ጊዜያት ኖሯል አሁን ለመቃብርም ይሁን ለሞት አዲስ ነገር ተፈጠረ ሲሞት ዓለምን ለማዳን ሲቀበር በሁለት ሰዎች ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሲነሳም ብቻው ልዩ ነገር ገጠማቸው በትንሣኤ

ስለዚህ የጌታ ትንሣኤ በኣራቱም ወንጌላውያን የትምህርታቸው መደምደሚያ ነበር።ማቴ 28፥1 ማር 16፥1 ሉቃ 24፥1 ዮሐ 20፥1 እነዚህ ምእራፎች እስከ ፍጻሚያቸው የትንሣኤውን ምስክርነት ጽፈዋል ኣንኣ ተነሣ እንደየት እንደ ሰገዱለት ተመዝግቧል

የክርስቶስ ትንሣኤ በወቅቱ ከተነሱ ሙታን የተለየ ነው።

፩ በጊዜው የተነሱ ሙታን ኣስነሽ ኣላቸው እንዲነሱ የሚጸልይ የሚለምን የሚያስነሳ ነበራቸው ለምሳሌ የመበለትዋ ልጅ።

“ ወደ እግዚኣብሔርም ኣቤቱ ኣምላኬ ሆይ የብላቴናው ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሀለሁ ብለው ብሎ ጮኸ“እግዚኣብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ የብላቴናውንም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች ፡፡1ኛ ነገ 17፥1_24

እዚህ እንዳየነው ሟች ካለ ሟች እንዲነሳ የሚለምን ኣለ ኣስነሽ ኣለ፡፡

“ እነሆ ኤልስዕ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ሕፃኑን ኣይኖቹን ከፈተ(ተነሣ)”

2ኛ ነገ 4፥32_37 የሞተ የሚማለድ የሚያስነሳ ኣለ፡፡

“ኤልሳዕም ሞተ ነበሩትም ከምኣብም ኣደጋ ጣዮች በየኣመቱ ወደ ሐገሩ ይገቡ ነበር ሰዎችም ኣንድ ሰው ሲቀብሩ ኣደጋ ጣዮችን ኣዩ ሬሳውንም በኤልሳ መቃብር ጣሉት የኤልሳዕን ኣጥንት በነካ ጊዜ ሰው ድኖ በእግሩ ቆመ ”2ኛ ነገ 13፥20

ከላይ እንደተመለከትነው እነዚህ ሁሉ ሙታን ኣስነሽ ይፈልጋሉ በራሳቸውም መነሣት ኣይችሉም የክርስቶ ስ ትንሣኤ ግን ከዚህ የተለየ ነው ኣስነሽ ኣያሻም በገዛ ስልጣኑ ነው የተነሣው” ይህን ቤተ መቅደስ ኣፍርሱት በሦስተኛውም ቀን እሰራዋለሁ” ዮሐ 2፥17_20

**፪ በብሉይ ሥጋ ነው የተነሱት**

ማለት እንደገና በሚታመም በሚደክም በሚራብ በሚጠማ በሚያንቀላፋ ሥጋ ነው የተነሱት ዳግመኛ ሞት ይጠብቃቸዋል ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ ግን በሐዲስ ሥጋ ነው ማለት መያዝ መጨበጥ መዳሰስ መታመም መድከም መራብ መጠማት ማንቀላፋት መሞት በማይስማማው ሥጋ ነው ሁለተኛ ሞት የለመትም

ከዚህ በኊላ ከኣምስት መቶ ለሚበዙ ሰዎች ታየ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ ኣሁን ኣሉ ኣንዳንዶች ግን ኣንቀላፍተዋል”1ኛ ቆሮ 15፥6 እነዚህ በዕለተ ዓርብ የተነሱ ናቸው ግን ተመልሰው የሞቱ እንደነበሩ ያሳያል

የክርስቶስ ትንሣኤ ግን ዳግም መሞት የለበትም ፍጹም ትንሣኤ ነውና እነዚህ ኤልያስ፥ ኤልስዕ፥ጌታችን ሐዋርያት ያስነሷቸው ሙታን በሙሉ ደግሞ ሞተዋል የሚኖሩትን ዘመን ኖረው ሞተዋል፡፡

የክርስቶስ ትንሣኤው ፍጹም ትንሣኤ በመሆኑ ዳግም ሞት የለበትም ፡፡ “ መሞትን ኣንድ ጊዜ ፈፅሞ ለኂጥያት ሞቷልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚኣብሔር ይኖራል ”ሮሜ 6፥10

**፫ እነዚህ ሁሉ ዳግም ሞት ኣለባቸው እንዳልን ዳግም ትንሣኤ ዘጉባኤን ይጠብቃሉ** እርሱ ግን ፈጥኖ ተነስቷል “ ወአህፀረ እድሜ ለርዕሱ ትንሣኤውን እድሜ ነበተ ጥሪኣን መጽሐ_በእዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች የክርስቶስ ትንሣኤ ልዩ ነው”

## የሰው ልጆች ትንሣኤ

የሰው ልጆች ትንሣኤ ዘጉባኤን ጠብቀው ለሚነሱት ትንሣኤ መሪው ወይም መሠረቱ የክርስቶስ ትንሣኤ ነው ክርስቶስ ሞትን ድል ኣድርጎ ትንሣኤያችንን ካበሠረ ጀምሮ የሰው ልጆች ሞትን መፍራት ትተዋል ይልቁም ወደ እርሱ ሄደው ከእግዚኣብሔር ጋር መኖርን መርጠዋል

“እምኒ ሐየውነ ለእግዚኣብሔር ነሐዩ ወዕመኒ ሞትነ ለእግዚኣብሔርን መውት ዕመኒ ሐየወነ ወእመኒ ሞትነ ለእግዚኣብሔር ጉደጋነ ብንኖርም ለእግዚኣብሔር እንኖራለን ብንሞትም ለእግዚኣብሔር እንሞታለን ብንሞትም ብንኖርም ለእግዚኣብሔር ነን”ሮሜ 14÷8

ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉም ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ፊል1÷3

የሰው ልጅ እንዲህ ከሞት ላይ ድፍረት ያገኘው ክርስቶስ በትንሣኤው ሌላ ሕይወት እንዳለ በማረጋገጡ ሞት በመሻሩ ነው።

ስለዚህ ሰው ይህን የክርስቶስን ትንሣኤ በኩር ኣድርጎ ከሙታን ተለይቶ ይነሣል ጻድቁም ኀጥዑም ይነሣ ዘንድ የግድ ነው የሰው ልጆችን ተስፋ ትንሣኤን የሚያሳዩ ትንቢቶችም ነበሩ

“የሰው ልጅ ሆይ እነዚህ ኣጥንቶች በሕይወት ይኖራሉን”ኣለኝ እኔም ጌታ ሆይ ኣንተ ታውቃለህ ኣልሁ እርሱም እንዲህ ኣለኝ በእነዚህ ኣጥንቶች ላይ ትንቢት ተናገር እንዲህም በላቸው እናንተ የደረቃችሁ ኣጥንቶች ሆይ የእግዚኣብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚኣብሔር ለእነዚህ ኣጥንቶች እንዲህ ይላል እነሆ ትንፋስን ኣለብሳችሁኣለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ ኣመትም እሰጣችኂለሁ ሥጋንም ኣወጣባችኂለሁ በእናንተም ላይ ቁርበትን እዘረጋለሁ ትንፋሽንም ኣነበላችኂለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ እኔም እግዚኣብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ።

እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ ስናገርም ድምፅ ሆነ እነሆም መናወጥ ሆነ ኣጥንቶችም ኣጥንት ከኣጥንት ጋር ተቀራረቡ እኔም ኣየሁ እነሆም ጅማት ነበረባቸው ሥጋም ወጣ ቁርበትም በላያቸው ተዘረጋ ትንፋሽ ግን ኣልነበረባቸውም እርሱም የሰው ልጅ ሆይ ትንቢት ተናገር ለነፋስም ትንቢት ተናገር ጌታ እግዚኣብሔር እንዲህ ይላል ነፋስ ሆይ ና ከኣራቱ ነፋሳት ዘንድ ና በተገደሉትም እነዚህ የተገደሉትም በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እፍ በልባቸው በል ኣለኝ እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ ትንፋሽም(ነፍስ)ገባባቸው ሕያዋንም ሆኑ እጅግ ትልቅ ሠራዊት ሆነው በእግራቸው ቆሙ ሕዝ 37÷3

ሕዝቤ ሆይ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁም ኣወጣችሁ ኣለሁ ሕዝቤ ሆይ መቃብራችሁን በከፈትኩ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኂችሁ ጊዜ እግዚኣብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ”ሕዝ 37÷12

ኣሁን ከላይ ያየነው የነብዩ የሕዝቅኤል ትንቢት በቀጥታ የሚያስረዳን የሰው ልጆች ሞተው ፈርሰው በስብሰው እንደማይቀሩ ትንሣኤ እንዳላቸው ነው ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ሙታንን የምታስተምረው የነቢያት ትንቢት የሐዋርያትን ትምህርትን መሠረት ኣድርጋ ነውና

ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹ ወደ እፍረት ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ጥበበኞችም እንድ ሰማይ ፀዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ “ዳን 12÷2

ቤተ ክርስቲያን ይህን ተስፋ ትንሣኤ ከነብያት እና ከሐዋርያት ኣግኝታ በሊቃውንት ታስተምራለች

ይህ ትንሣኤ ዘጉባኤ በሚሆንበት ጊዜ ንቃህ መዋቲ ዘትነው ወያበርህ ለከ ክርስቶስ ኣንተ የተኛህ ንቃ ክርስቶስ ያበራልሃል" እንደተባለው ቅዱስ እግዚኣብሔር ዘያነቅሆሙ ለሙታን ሙታንን የሚያስነሳቸው እግዚኣብሔር ልዩ ነው የሚለው ኣዋጅ ሲታወጅ ኣውሬ የበላው ውሃ የወሰደው የፈረሰ የበሰበሰው የሥጋ ቅሪት ሁሉ ይሰበሰባል

በቀዳሚ ነፍሐተ ቀን ሣትግ በዕኩሉ ፀበለ ሥጋ ዘተዘርው ውስተ ኩሉ ኣጽናፈ ዓለም ዘበልየ ወዘማሰነ በዘዚኣሁ ኣሪያ ወኣምሳል ወበዳግም ንፍሐተ ቀን ይሰፈያ አዕጽምት ምስለ ሥጋ ወሣከውን ንፍሐተ ቀን ይትነሰኡ ሙታን ጻድቃን ወኃጥኣን እንዘ ይፀውሩ ምግባራቲሆሙ እማሂ ሰናየ ወእመሂ እኩይ ዘተለዎሙ እምዲበምድር

በመጀመሪያ የነጋሪት ድምፅ በዓለም ዳርቻ በተነ ኣጥንት ሁሉ ውሃ የወሰደው በኣራዊት ሆድ ውስጥ ያለው በልዩ ልዩ መልኩ የጠፋው ኣጥንት ይሰበሰባል

በሁለተኛ የነጋሪት ድምፅ ያለመንቀሳቀስ ትኩስ በድን ይሆናል

በሦስተኛው የነጋሪት ድምፅ ጻድቃንም ኃጥኣንም ከምድር የተከተላቸውን ሥራቸውን ይዘው እንደ ዓይን ጥቅሻ ይነሳሉ" ያዕ

- ጻድቁም ሥራውን ይዞ ይነሣል ዋጋውን የሚቀበልበት ነውና
- ኃጥኡም ሥራውን ይዞ ይነሣል ፍዳውን የሚቀበልበት ነውና

ገበሬ ጤፍ ዘርቶ ኑግ  ኑግ ዘርቶ ጤፍ ማጨድ እንደማይችል ሁሉ ጻድቁ ኃጥእ ኃጥሁ ጻድቅ ሆኖ ኣይነሳም ቅዱስ ጳውሎስ ትንሣኤ ሲያስተምር

አአበድ አንተ ዘትዘርእ ኢየሐዩ ለእመ ኢሞተ አንተ ሠነፍ አንተ የዚሁኽው ዘር ካልፈረሰ ካልበሰበሰ አይበቅልም ብሎ ያስተማረው ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዎች ስለነበሩ ነው 1ኛ ቆሮ 15፥1_9

ጌታችንም የሙታንን ትንሣኤ እንዲህ በማለት ነግሮናል ኣማን እብለክ ይበድህ ጊዜ ከመምውታን ይስምዕዎ ቃሎ ለወልደ እግዚአብሔር ወይዕዜ ውእቱ ወይወጽኡ እለሰናየ ገብሩ ውሰተ ትንሣኤ ዘለህይወት ወእለሰ እኩየ ገብሩ ውስተ ትንሣኤ ዘለጸይን "እውነት እላችኋለሁ ሙትን የእግዚአብሔርን ልጅ ቃል የሚሰሙበት ግዜ ይመጣል እርሱም አሁን ነው ። መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉ የሰሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይነሣሉ" ዮሐ 5፥26

የሰው ልጆች የመጨረሻ ተስፋ ትንሣኤ ዘጉባኤን ጠብቆ ተነስቶ መንግስቱን መውረስ ነው።

ከዚህ በኂላ ሞት የለም ሀዘን ልቅሶ መቃብር የለም የሕይወት ትንሣኤ ለሚነሱ ይህንም ትንሣኤ የሚያገኙ የመጀመሪያውን ትንሣኤ ልቡና የተነሱ ናቸው ማለት ያመኑ የተጠመቁ ናቸው።

"ይህ የፊተኛው ትንሣኤ እድል ፈንታ ያለው ብፁዕ እና ቅዱስ ነው ሁለተኛው ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውምና"ራዕ 20፥6

ሁለተኛው ሞት የፍርድ ትንሣኤ ሲሆን ላላመኑት ሁሉ የተሰጠ ነው ለሚያምኑት ይህ የለም መልካም ይሠራሉና። መልካም ሠርተን መንግስቱን እንድንወርስ ይርዳን

ስለዚህ የጌታ ትንሣኤ በአራቱም ወንጌላውያን የትምህርታቸው መደምደሚያ ነበር።ማቴ 28፥1 ማር 16፥1 ሉቃ 24፥1 ዮሐ 20፥1 እነዚህ ምዕራፎች እስከ ፍጻሜያቸው የትንሣኤውን ምስክርነት ጽፈዋል እንደተነሣ እንዳዩት እንደሰገዱለት ተመዝግቧል።

**የክርስቶስ ትንሣኤ በወቅቱ ከተነሱ ሙታን የተለየ ነው።**

**፩ በጊዜው የተነሱ ሙታን አስነሽ አላቸው። እንዲነሱ የሚጸልይ፤ የሚለምን፤ የሚያስነሳ ነበራቸው ለምሳሌ የመበለትዋ ልጅ።**

“ ወደ እግዚአብሔርም አቤቱ አምላኬ ሆይ የብላቴናው ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሀለሁ ብሎ ጮኸ“እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች። 1ኛ ነገ 17፥1_24 እዚህ እንዳየነው ሟች አለ ሟች እንዲነሳ የሚለምን አለ አስነሽ አለ።

“ እነሆ ኤልስዕ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ሕፃኑ አይኖቹን ከፈተ(ተነሣ)”2ኛ ነገ 4፥32_37

የሞተ የሚማለድ የሚያስነሳ አለ።

“ኤልሳዕም ሞተ ቀበሩትም ከሞአብም አደጋ ጣዮች በየዓመቱ ወደ ሀገሩ ይገቡ ነበር ሰዎችም አንድ ሰው ሲቀብሩ አደጋ ጣዮችን አዩ ሬሳውንም በኤልሳዕ መቃብር ጣሉት የኤልሳዕን አጥንት በነካ ጊዜ ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ ”2ኛ ነገ 13፥20

ከላይ እንደተመለከትነው እነዚህ ሁሉ ሙታን አስነሽ ይፈልጋሉ በራሳቸውም መነሣት አይችሉም የክርስቶስ ትንሣኤ ግን ከዚህ የተለየ ነው አስነሽ አያሻም በገዛ ስልጣኑ ነው የተነሣው” ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን እሰራዋለሁ” ዮሐ 2፥17_20

**፪ በብሉይ ሥጋ ነው የተነሱት**

ማለት እንደገና በሚታመም በሚደክም በሚራብ በሚጠማ በሚያንቀላፋ ሥጋ ነው የተነሱት ዳግመኛ ሞት ይጠብቃቸዋል ማለት ነው ። ክርስቶስ ግን በሐዲስ ሥጋ ነው ማለት መያዝ፤ መጨበጥ፤ መዳሰስ፤ መታመም፤ መድከም፤ መራብ፤ መጠማት፤ ማንቀላፋት፤ መሞት በማይስማማው ሥጋ ነው ሁለተኛ ሞት የለበትም።

ከዚህ በኃላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ሰዎች ታየ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል”1ኛ ቆሮ 15፥6 እነዚህ በዕለተ ዓርብ የተነሱ ናቸው ግን ተመልሰው የሞቱ እንደነበሩ ያሳያል የክርስቶስ ትንሣኤ ግን ዳግም መሞት የለበትም ፍጹም ትንሣኤ ነውና እነዚህ ኤልያስ፥ ኤልስዕ፥ጌታችን ሐዋርያት ያስነሷቸው ሙታን በሙሉ የሚኖሩትን ዘመን ኖረው ሞተዋል።

የክርስቶስ ትንሣኤው ፍጹም ትንሣኤ በመሆኑ ዳግም ሞት የለበትም

“ መሞትን አንድ ጊዜ ፈፅሞ ለኃጢአት ሞቷልና በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል”ሮሜ 6፥10

**፫እነዚህ ሁሉ ዳግም ሞት አለባቸው እንዳልን ዳግም ትንሣኤ ዘጉባኤን ይጠብቃሉ እርሱ ግን ፈጥኖ ተነስቷል**

“ወአህፀረ እድሜ ለርዕሱ”ማለትም“የትንሣኤውን እድሜ ፈጥኖአደረገ”እንዲልን መጽሐፍበእዚህ መሠረታዊ ጉዳይ የክርስቶስ ትንሣኤ ልዩ ነው”

## የሰው ልጆች ትንሣኤ

የሰው ልጆች ትንሣኤ ዘጉባኤን ጠብቀው ለሚነሱት ትንሣኤ መሪው ወይም መሠረቱ የክርስቶስ ትንሣኤ ነው። ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ትንሣኤያችንን ካበሠረ ጀምሮ የሰው ልጆች ሞትን መፍራት ትተዋል ይልቁም ወደ እርሱ ሄደው ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን መርጠዋል።

"እመኒ ሐየውነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ፡ ወዐመኒ ሞትነ ለእግዚአብሔርንመውት፡ ዕመኒ ሐየውነ ወእመኒ ሞትነ ለእግዚአብሔር ንሕነ"ይህም"ብንኖርም ለእግዚአብሔር እንኖራለን ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን ብንሞትም ብንኖርም ለእግዚአብሔር ነን"ሮሜ 14፥8

ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉም ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ፊል1፥3

የሰው ልጅ እንዲህ ከሞት ላይ ድፍረት ያገኘው ክርስቶስ በትንሣኤው ሌላ ሕይወት እንዳለ በማረጋገጡ ሞት በመሻሩ ነው።

ስለዚህ ሰው ይህን የክርስቶስን ትንሣኤ በኩር አድርጎከሙታን ተለይቶ ይነሣል ጻድቁም ኃጥዑም ይነሣ ዘንድ የግድ ነው የሰው ልጆችን ተስፋ ትንሣኤን የሚያሳዩ ትንቢቶችም ነበሩ።

"የሰው ልጅ ሆይ እነዚህ አጥንቶች በሕይወት ይኖራሉን"አለኝ እኔም ጌታ ሆይ አንተ ታውቃለህ አልሁ እርሱም እንዲህ አለኝ በእነዚህ አጥንቶች ላይ ትንቢት ተናገር እንዲህም በላቸው እናንተ የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል እነሆ እስትንፋስን አሳድርባችኋለውበሕይወትም ትኖራላችሁ አጥንትም እሰጣችኃለሁ ሥጋንም አወጣባችኃለሁ በእናንተም ላይ ቁርበትን እዘረጋለሁ ትንፋሽንም አገባባችኋለው በሕይወትም ትኖራላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ።

እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ ስናገርም ድምፅ ሆነ እነሆም መናወጥ ሆነ አጥንቶችም አጥንት ከአጥንት ጋር ተቀራረቡ እኔም አየሁ እነሆም ጅማት ነበረባቸው ሥጋም ወጣ ቁርበትም በላያቸው ተዘረጋ ትንፋሽ ግን አልነበረባቸውም እርሱም የሰው ልጅ ሆይ ትንቢት ተናገር ለነፋስም ትንቢት ተናገር ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነፋስ ሆይ ና ከአራቱ ነፋሳት ዘንድ ና በተገደሉትም እነዚህ የተገደሉትም በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እፍ በልባቸው በል አለኝ እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ ትንፋሽም(ነፍስ)ገባባቸው ሕያዋንም ሆኑ እጅግ ትልቅ ሠራዊት ሆነው በእግራቸው ቆሙ ሕዝ 37፥3

ሕዝቤ ሆይ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁም አወጣችኋለው ሕዝቤ ሆይ መቃብራችሁን በከፈትኩ ጊዜ ከመቃብራችሁም ባወጣኋችሁ ጊዜ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ"ሕዝ 37፥12

አሁን ከላይ ያየነው የነብዩ የሕዝቅኤል ትንቢት በቀጥታ የሚያስረዳን የሰው ልጆች ሞተው ፈርሰው በስብሰው እንደማይቀሩ ትንሣኤ እንዳላቸው ነው ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ሙታንን የምታስተምረው የነቢያትን ትንቢት የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት አድርጋ ነውና።

ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹ ወደ እፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ጥበበኞችም እንደ ሰማይ ፀዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ ዳን 12፥2

ቤተ ክርስቲያን ይህን ተስፋ ትንሣኤ ከነቢያት እና ከሐዋርያት አግኝታ በሊቃውንት ታስተምራለች

ይህ ትንሣኤ ዘጉባኤ በሚሆንበት ጊዜ "ንቃህ መዋቲ ዘትነውም፡ ወያበርህ ለከ ክርስቶስ""አንተ የተኛህ ንቃ ክርስቶስ ያበራልሃል" እንደተባለው ቅዱስ እግዚአብሔር ዘያነቅሆሙ ለሙታን ሙታንን የሚያስነሳቸው እግዚአብሔር ልዩ ነው የሚለው አዋጅ ሲታወጅ አውሬ የበላው፤ ውሃ የወሰደው፤ የፈረስ የበሰበሰው ፤የሥጋ ቅሪት ሁሉ ይሰበሰባል

በቀዳሚ ነፍሐተ ቀርን ይትጋባዕኩሉ ፀበለ ሥጋ ዘተዘርወ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ዘበልየ ወዘማሰነ በዘዘ ዚአሁ አርአያወአምሳል ወበዳግም ንፍሐተ ቀን ይሰፈያ አዕጽምት ምስለ ሥጋ ወይከውን በድነፍጹመዘእንበለአንሳሕስሆወኢተሐውሶእስከጊዜሁወበሣልስንፍሐተ ቀርን ይትነስኡ ሙታን ጻድቃን ወኃጥአን እንዘ ይፀውሩ ምግባራቲሆሙ እመሂ ሰናየ ወእመሂ እኩየ ዘተለዎሙ እምዲበምድር

በመጀመሪያ የነጋሪ ት ድምፅ በዓለም ዳርቻ የተበተነ አጥንት ሁሉ ውሃ የወሰደው በአራዊት ሆድ ውስጥ ያለው በልዩ ልዩ መልኩ የጠፋው አጥንት ይሰበሰባል

በሁለተኛ የነጋሪት ድምፅ ያለመንቀሳቀስ ትኩስ በድን ይሆናል

በሦስተኛው የነጋሪት ድምፅ ጻድቃንም ኃጥአንም ከምድር የተከተላቸውን ሥራቸውን ይዘው እንደ ዓይን ጥቅሻ ይነሳሉ" ያዕቆብ ዘሥሩግ

- ጻድቁም ሥራውን ይዞ ይነሣል ዋጋውን የሚቀበልበት ነውና
- ኃጥኡም ሥራውን ይዞ ይነሣል ፍዳውን የሚቀበልበት ነውና

ገበሬ ጤፍ ዘርቶ ኑግ ኑግ ዘርቶ ጤፍ ማጨድ እንደማይችል ሁሉ ጻድቁ ኃጥእ ኃጥኡ ጻድቅ ሆኖ አይነሳም ቅዱስ ጳውሎስ ትንሣኤ ሙታንን ሲያስተምር ኦ አብድ አንተ ዘትዘርእ ኢየሐዩ ለእመ ኢሞተ አንተ ሠነፍ አንተ የዘራኸው ዘር ካልፈረሰ ካልበሰበሰ አይበቅልም ብሎ ያስተማረው ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዎች ስለነበሩ ነው 1ኛ ቆሮ 15፥1_9

ጌታችንም የሙታንን ትንሣኤ እንዲህ በማለት ነግሮናል አማን እብለክሙከመይበጽሕጊዜሁ ከመምውታን ይሰምዕዎ ቃሎ ለወልደ እግዚአብሔር ወይዕዜ ውእቱ ወይወጽኡ እለሰናየ ገብሩ ውስተ ትንሣኤ ዘለህይወት ወእለሰ እኩየ ገብሩ ውስተ ትንሣኤ ዘለደይን "እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ቃል የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል እርሱም አሁን ነው።

መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉ የሰሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይነሣሉ" ዮሐ 5፥26

የሰው ልጆች የመጨረሻ ተስፋ ትንሣኤ ዘጉባኤን ጠብቆ ተነስቶ መንግሥቱን መውረስ ነው።

ከዚህ በኋላ ሞት የለም፤ ሀዘን ልቅሶ መቃብር የለም፤ የሕይወት ትንሣኤ ለሚነሱ ይህንም ትንሣኤ የሚያገኙ የመጀመሪያውን ትንሣኤ ልቡና የተነሱ ናቸው ማለት ያመኑ የተጠመቁ ናቸው።

"ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው ፤ በዚህእድል ፈንታ ያለው ብፁዕ እና ቅዱስ ነው ሁለተኛው ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውምና"ራዕ 20፥6

ሁለተኛው ሞት የፍርድ ትንሣኤ ሲሆን ላላመኑት ሁሉ የተሰጠ ነው ለሚያምኑት ግንይህ የለም መልካም ይሠራሉናመልካም ሠርተን መንግስቱን እንድንወርስ ይርዳን።

ስብሐት ለአምላክ አበዊነ። አሜን!!!

## ዋቢመጻሕፍት

- መጸሐፍቅዱስ 81
- አምስቱ አዕማደ ምስጢር
- የኢትዮጵያ እምነት በሶስቱ ሕግጋት - አያሌውታምሩ (አለቃ)
- መድሎተ አሚን - አድማሱጀምበሬ (መልአከብርሃን)
- አንድምታ ኦሪት ዘፍጥረት - ትንሳኤዘጉባኤ
- የመምህር ምስጢረሥላሴ የግልማስታወሻ

አዘጋጅ፡ መምህር ምስጢረሥላሴ ማናዬ

ቀን፡ ፲፪መጋቢት፳፻፲ዓ.ም

ቦታ፡ ፕሪቶርያ - ደቡብአፍሪካ

ጽሁፉን በመጻፍ የተባበሩኝ፡ ዶ/ር ንዋይ (ተክለሐና)፤ ሲስተርትግስት (ፍቅርተማርያም)፤ ሲስተርጽጌረዳ